# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፒትስት ቤ/ክ

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

# መጽሐፈ መሳፍንት

## ክፍል አንድ

## ለቤት ለቤት ህብረቶች

## ትምህርትና ሥልጠና ክፍል

**January 2021**

**Ethiopian Evangelical Baptist Church**

**3001 Saturn rd, Garland, TX, 75041**

**Phone- 214-227-1911/214-703-0100**

**Fax: (972)-271-6445**

**www.eecdallas.org**

## ቡራኬና ምስጋና

ከዚህ በታች ያሉትን የአገልግሎት ክፍሎችና ወገኖችን እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ እንላለን

1. ጥናቶችን በትጋት እያዘጋጁ ያሉትን አገልጋዮች በሙሉ
2. የቤት ለቤት ህብረቶችን በማስተባበር እየተጉ ያሉትን አገልጋዮች
3. የቤት ለቤት ህብረቶችን በመምራት የሚተጉትን መሪዎችን
4. በቤት ለቤት ህብረቶች እየተሳተፉ ያሉትን ወገኖች
5. የእግዚአብሔር ቃል እንዲጠና ቤታቸውን የሰጡትን ወገኖች እና
6. የቤተ ክርስቲያናችንን መሪዎች

በጸሎታችን ሁልጊዜ አንረሳችሁም! እናንተም እንዲሁ አስቡን።

## ጠቃሚ ማሳሰቢያዎች፡-

1. የመሳፍንትን መጽሐፍ ሙሉውን እና ኢያሱ 21-24 እንዲታነቡ በትልቅ ትህትና እንጠይቃለን።
2. ለአንድ ቀን የተዘጋጁ ጥናቶች በዕለቱ መጨረስ ካልተቻለ ለሁለት የጥናት ቀና ማድረግ ይቻላል።
3. የመሳንፍንት መጽሐፍ 21 ምዕራፎች ሲኖሩት ከታሪኩ ይዘት የተነሳ መጽሐፉ ሁለት የጥናት ክፍሎች ይኖሩታል ማለትም መሳፍንት ከምዕራፍ 1:1- ምዕራፍ 3:6 እና መሳፍንት ምዕራፍ 17- ምዕራፍ 21 የመሳፍንት መጽሐፍ ጥናት ክፍል አንድ ሲሆን ከመሳፍንት ምዕራፍ 3:7- ምዕራፍ 16:31 ያለው ክፍል ደግሞ ክፍል ሁለት ጥናት ይሆናል። ይህኛው ጥናት የመጀመሪያው ክፍል ይሆናል።

# መጽሐፈ መሳፍንት
# የመግቢያ ጥናት
# ጥናትአንድ
# የመሳፍንትን መጽሐፍ ማጥናት
# ለምን አስፈለገ?

ከዚህ በፊት ስለነበሩን ጥናቶች እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። አሁን ደግሞ በዚህ ጊዜ የምናጠናው ከብሉይ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍት መካከል አንዱ የሆነውን የመሳፍንትን መጽሐፍ ይሆናል።

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ለመንፈሳዊ ህይወት መመሪያ የሚሰጡ መጽሐፍት እንደሆኑ ማስረጃዎች በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶ እናገኛቸዋለን። ከእነዚህም መካከል ሁለቱ ከዚህ በታች ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን።

> “አንተ ግን በተማርኸውና በተረዳኸው ጽና፤ ይህን ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ 15ከሕፃንነትህም ጀምረህ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል። 16ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሥጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ 17ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው” (2ጢሞ 3:14-17)።
>
> “ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጒመው አይደለም፤ 21 ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው

ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም" (2ጴጥ 1:20-21)።

ስለዚህም 39ኙ የብሉይ ኪዳን እና 27ቱ የአዲስ ኪዳን በጠቅላላው 66ቱም ቅዱሳን መጽሐፍት ለትምህርታችን እና ለጥቅማችን እንደተጻፉ እናምናለን።

ቀጥታ ወደ መሳፍንት መጽሐፍ ከመሸጋገራችን በፊት ስለ መጽሐፈ ኢያሱ ማወቅ በጣም ጥሩ ይሆናል። በኢያሱ ዘመን የምናያቸው የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የጨከኑ፥ በስሜታቸውና በራሳቸው እይታ ሳይሆን በእግዚአብሔር እይታ ነገሮችን የሚያዩ ነበሩ። ኢያሱ ከሞተ በኋላ ግን ይህ ተለወጠ። ከመሳንፍት ዘመን ጀምሮ የእስራኤል ልጆች ለዘመናት የቀጠለ ውድቀት ውስጥ የገቡት።

በመሳፍንት መጽሐፍ አንድ ወሳኝ ዐረፍተ ነገር ተጽፎ እናገኛለን። ይህም እንደሚከተለው ይላል "የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነ ነገር አደረጉ" የሚለው ነው (በምዕ 2፡11 )። በመጽሐፉ መደምደምያ ላይ ደግሞ ያለ ወሳኝ ዐረፍተ ነገር "ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" የሚለው ነው (በምዕ 17፡6 ) እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የተያያዙ ናቸው። እነርሱንም ለመረዳት መጀመሪያ ማየት ያለብን "በእግዚአብሔር ፊት" የሚለውን ቃል ነው። ይህ በእግዚአብሔር አይን "ክፉ" የሆነው ነገር ግን፥ በእስራኤል ልጆች እይታ "መልካም" የሚመስል ነበር።

የመሳፍንት ዘመን ዋነኛ ችግር የእስራኤል ልጆች የሚያደሪጉትን ነገር ወይም የሚኖሩትን ኑሮ የሚመዝኑበት መመዘኛ የተነገራቸው የእግዚአብሔር ህግ (ቃል) ሳይሆን የራሳቸው ውስን አስተሳሰብ ወይም

ስሜት መሆኑ ነበር (“ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን”)። ችግራቸው እራሳቸውን ከጣኦት አምላኪ ህዝብ ጋር ማነጻጸር ነበር። የእነዚህ ሰዎች ሀሳብ ከእግዚአብሔር ህግ ጋር ተቃራኒ ነበር።

ወደ ጥናቱ ስንገባ የመሳፍንትን መጽሐፍ በዚህ ባለንበት ጊዜ/ዘመን ማጥናት የሚያስፈልግበት ምክንያት፤ አሁን ያለንበት ዘመን በብዙ የመሳፍንት ዘመንና ስለሚመሳሰል ነው። ተመሳሳይነቱንም በጥቅሉ እንደሚከተለው መግለጥ ይቻላል። አሁን ባለንበት ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች ነን ብለን እራሳችንን ብንጠራም አንዳንዶቻችን ወይም ብዙዎቻችን የምንኖረው ኑሮ ግን ለእኛ ስሜት የሚመች፥ በእኛ መመዘኛ ልክ የመሰለንን፥ “ምን አለበት” እያልን እንጂ፥ “የእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም ነው? ወይንስ ቃሉስ ምን ይላል?” እያልን አይደለም።

እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይነት ስላለ፥ የመሳፍንትን መጽሐፍን በማጥናት ስለ ጸሎት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለማወቅና ስለመታዘዝ ፥ ስለንስሃ፥ ስለቅዱሳን ህብረት፥ ስለምስክርነት፥ ስለቤተሰብ፥ ስለአገልግሎት ወዘተ እናያለን። በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ብዙ የሚያስተምረን፥ የሚገሥጽን፥ የሚያስተካክለን፥ የሚያበረታታን ነገሮች እናገኛለን። በመሳፍንት ዘመን ከነበሩት ስህተት ልንማርና ብዙ ማስተዋል ሆኖልን እኛም ተጠቅመን ከእኛም አልፎ ሌሎችንም ማክፈልና መርዳት የምንችል እንሆናለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመግቢያ ላይ በተጠቀሰው ሁለት ጥቅሶች መሠረት የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት በአዲስ ኪዳን ዘመን ማጥናት አስፈላጊነቱ ለምንድ ነው?
2. በመግቢያው መሠረት የመሳፍንትን መጽሐፍ አሁን ማጥናት ለምን አስፈለገን?

3. መሳፍንት 2:11 እና 17:6ን በማንበብ ስለ መሳፍንት ዘመን እንዴት ይገልጸዋል?
4. በመግቢያው መሠረት የመሳፍንት ዘመን ታሪክ ከእኛ ዘመን ጋር ምን ግንኙነት አለው?
5. በዚህ ባለንበት ዘመን ከመሳፍንት ዘመን ሰዎች ህይወት ጋር የሚመሳሰልበትን ምሳሌዎችን በመጥቀስ ተወያዩ
6. በመጨርሻም በሚቀጥሉት የጸሎት ርዕሶች ላይ እንጸልይ፦
   - በዚህ ጥናት ጌታ መንፈሳዊ ዓይናችንን እንዲያበራ እና መጽሐፉን የማንበብ ጥማት እንዲሰጠን እንጸልያለን።
   - በዚህ መጽሐፍ ጥናት ጊዜ ማንኛውንም መሰናክሎችን እግዚአሔሪ ከፍታችን እንዲያነሳ እንጸልያለን።
   - ለህብረታችን ጥንካሬ እና ጌታ ሁል ጊዜ በመገኘቱ እንዲባርከንና ሌሎችም ንሰሃና ድነትን እንዲያገኙ እንጸልያለን።
   - ስለቡድናችን አባላት አስጠኚ፥ እንዲሁም ስለሌሎች የጥናት ቡድኖች እንጸልያለን ።

# ጥናት ሁለት
# የተስፋ ቃል ጠባቂ አምላክና ህዝቡ
# የምንባብ ክፍል:- ኢያሱ 21፡43-22፡6

**የጥናቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ጠባቂነት ማሳየትና ሰውም የገባውን ቃል ኪዳን ጠባቂ ሊሆን እንደሚገባው ማስገንዘብ።

**መግቢያ፡-** የመሳፍንት መጽሐፍ የኢያሱ 21፡43-24:33 ቀጣይ ታሪክ እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ የኢያሱ 21፡43-24:33 የመሳፍንት ታሪክ የመግቢያው ጥናት ሆኖ ያገለግላል ። በዛሬው ጥናት ማለትም በኢያሱ 21፡43-22:34 ባለው ክፍል ታሪክ በኢያሱ ዘመን እግዚአብሔር እንዴት የተስፋ ቃሉን እንደጠበቀና እስራኤላውያንም የራሳቸውን ድርሻ እንዴት እንደጠበቁ እናያለን።

በኢያሱ መጽሐፍ መደምደሚያ ላይ የነበሩ እስራኤላዊያን እና በመሳፈንት ዘመን የነበሩ ግንኙነታቸውን በትክክል ያነጻጽራል። ስለዚህ የኢያሱን የመጨረሻውን ክፍል ታሪክ ማወቅ ለመሳፍንት መጽሐፍት እጅግ አስፈላጊ ነው። ታሪኩ በጣም የተቆራኙ እንደሆነ ማወቅ ይጠቅማል።

## የክፍሉ አጭር ማብራሪያ-(የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እና የእስራኤላዊያን ኃላፊነት)

ኢያሱ 21፡43-45 ዋና መልዕክቱ እግዚአብሔር ለእስራኤል አባቶች (ለአብርሐም፣ለይስሐቅ እና ለያዕቆብ) የገባውን ቃል ኪዳን በኢያሱ ዘመን ለነበሩት እስራኤላውያን መፈጸሙን ነው። ከተናገረው ያልተፈጸመ አንዳችም ነገር የለም ይለናል።

**ኢያሱ 21፡43-22፡6** የኢያሱ መጽሐፍ መደምደምያ ከመሳፍንት መጽሐፍት ጥናት የመጀመርያ ክፍል ተደርጎ መውሰድ ይቻላል። ይህ መደምደምያ ወደ ኋላ ዞር ብሎ በመጽሐፉ ውስጥ የተፈጸሙትን ክስተቶች ከምዕራፍ አንድ አንጻር የሚገመግም ነው። ሁለት ዓይነት ግምገማዎች በዚህ ክፍል ተጽፈዋል፡- 1) 21፡43-45 እግዚአብሔርን ኢያሱ 1፡2-6 ባለው መሠረት የሚገመግም ሲሆን-ማለትም እግዚአብሔር ቃል በገባላቸው መሠረት ድል እንደሰጣቸው 2) 22፡1-6 ሁለት ከግማሽ የሆኑ ነገዶችን ከኢያሱ 1፡12-18 አንጻር ይገመግማል። በኢያሱ 1፡12-18 የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንደተወጡ በኢያሱ 22፡1-6 ይናገራል።

አንዳንድ ሰዎች በኢያሱ 21:43-45 ያለውን ከኢያሱ 13፡1 ጋር በማነጻጸር ግራ ይጋባሉ። ይሁን እንጂ በኢያሱ 13፡1 እግዚአብሔር ራሱ ገና እስራኤል ያልወረሰው መሬት እንዳለ ለኢያሱ ይነግረዋል። ታዲያ ገና ያልተወረሰ መሬት ካለ እንዴት የተስፋ ቃሉ ተፈጸመ ይለናል? ይህን ለመረዳት ኢያሱ 1፡3ን በአግባቡ መረዳት ተገቢ ነው። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር የገባዋው ቃል “እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ” ነው የሚለው። ይህ ማለት ወደ ተመደበላቸው ቦታ ሄደው በመዋጋት ለማስለቀቅ የራሳቸው ድርሻ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ፥ ያ ቦታ የእነርሱ ሆኗል። በመታዘዝ ተዋግተው የተሸነፉበት እና ያልወረሱት ቦታ የለም።

**ኢያሱ 22፡1-6** ዋና መልዕክቱ የሮቤል፣የጋድና የምናሴ እኩሌታ ነገዶች በኢያሱ 1፡12-18 የገቡትን ቃል መፈጸማቸውን ነው። እነዚህ ሁለት ከግማሽ የሆኑ ነገዶች በሙሴ ጊዜ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ

ቦታ ተሰጥቶአቸዋል። ይህ የተሰጣቸው ቦታ እስራኤል ሁሉ በሙሴ መሪነት ተዋግተው በቁጥጥር ስር ያዋሉት ቦታ ነው። በቁጥጥር ስር ቢውሉም ግን፥ ገና በሌሎች ህዝቦች የተያዙ ቦታዎች እንዳሉአቸው ኢያስ 13 ይነግረናል። እነዚህ ነገዶች ሌሎቹን የእስራኤል ነገዶች የረዱአቸው ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ያለውን ምድር እንዲቆጣጠሩ መርዳት ብቻ ነው። አሁን ወንድሞቻቸውም እንደእነርሱ በራሳቸው የእያንዳንዳቸውን ክልል ከጠላት እያስለቀቁ እንዲወርሱ ሃላፊነት አለባቸው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢያሱ 1፡3 መሠረት "እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ" የሚለውን ሀሳብ እንዴት እንደተረዳችሁ ተወያዩ? ይህንን ተስፋ ለመውረስ እነርሱ መዋጋት ለምንድ ነው የሚጠበቅባቸው?
2. ኢያሱ 13፡1 ከኢያሱ 1፡3 ጋር በማነጻጸር ለምን ያልተወረሰ ቦታ እንደቀረ ተነጋገሩ።
3. ኢያሱ 21፡43-45 መሠረት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ ስለመፈጸሙ ምን ትረዳላችሁ?
4. በዚህ ዘመን "የረገጥነውን እንወርሳለን ወይም እወርሳለሁ!" የሚለው ሀሳብ ችግሩ ምንድ ነው?
5. በኢያሱ 21፡44 መሠረት የእግዚአብሔርንና የእስራኤዊያን ድርሻ እንዴት እንደተገለጠ ተወያዩ።
6. በኢያሱ 1፡16-18 የሮቤል፥ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ለኢያሱ የገቡትን ቃል ምንድ ነው?

7. ኢያሱ 22፡1-5 በማንበብ ስለ እነዚህ ነገዶች ቃላቸውን ጠባቂነታቸውን ተነጋገሩ፤ ከዚህስ ምን እንማራለን?
8. እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋ እና በእኛ ኃላፊነት መካከል ያለውን አንድነት በስፋት ተነጋገሩ?
9. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን?

***መደምደምያ፡-***

እግዚአብሔር ለግላችን፥ ለቤተሰቦቻችን፥ ለቤተክርስትያንና ለሀገራችን የሰጠውን የተሰፋ ቃል እንደሚጠብቅ እያመንን፥ የእኛን ድርሻ ለእርሱ በመታዘዝ በመኖር፣ በቅድስና ህይወት በመመላለስ የጌታን ፈቃድ በማድረግ ኃላፊነታችንን እንወጣለን።

# ጥ ና ት ሶ ስ ት
# የ ተ ፈ ተ ነ ህ ዝ ብ
## የ ም ን ባ ቡ ክ ፍ ል፡- ኢያሱ 22፡7-34

**የጥናቱ ዓላማ**

እስራኤላዊያን ያለ ኢያሱ መሪነት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖራቸውን በማሳየት አማኞች በእግራቸው ቆመው የሚመጣባቸውን ፈተና ኃላፊነት ሊወጡ እንደሚገባ ማስገንዘብ

**መግቢያ**

በኢያሱ መሪነት እስራኤል የከነዓንን ምድር ከጠላት በማስለቀቅ እንደተቆጣጠሩት ነገር ግን በከነዓን ምድር ገና የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦች እንዳሉ በባለፈው ጥናት አይተናል። በዚህ ጥናት (ኢያሱ 22፡7-34) ደግሞ ኢያሱ ሲሞት ህዝቡ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ህይወት መቀጠል እንዲችሉ ይቀጥሉ ወይስ አይቀጥሉ የሚለውን ኢያሱ ፈትኖ ያየበትን ታሪክ እናያለን።

## የክፍሉ ታሪክ አጭር ማብራሪያ (ኢያሱ 22፡7-34)

**በኢያሱ 22፡7-34** ይህ ክፍል የሚተርከው እስራኤላዊያን ከአህዛብ ጋር የነበራቸውን የኃጢአት ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በመካከላቸውም ያነበረውን አለመታዘዝ፣ ኃጢአትና ዓመጻ ላይ መጨከን እንዳለባቸው ይናገራል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ልዩነቱ እርሱን መታዘዝ ብቻ ነው።

**ኢያሱ 22፡7-9** ኢያሱ ሁለት ከግማሽ (ሮቤል፣ጋድ እና የምናሴ ግማሽ) የሆኑትን ነገዶች ከምርኮ ከተገኘው ሀብት በመስጠት ባርኮ

ከዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው ምድር ላካቸው ወይም መለሳቸው።
የሰጣቸውንም ሀብት ከወንድሞቻቸው ጋር እንዲካፈሉት አዘዛቸው።

**ኢያሱ 22፡10-12** ይህ ክፍል እንደሚነግረን ሁለት ከግማሽ የሆኑትን ነገዶች (ሮቤል፣ጋድ እና የምናሴ ግማሽ) ከወንድሞቻቸው ጋር እንዲካፈሉት የተሰጣቸውን ከምርኮ የተገኘውን ሀብት "መሰዊያ" ለመስራት ተጠቀሙበት። የተቀሩትም ነገዶች ይህን በሰሙ ጊዜ እነዚህን ነገዶችን በሰይፍ ለማጥፋት ተነስተው መሰዊያው ወደተሰራበት ቦታ ሄደዋል ነገር ግን በኢያሱ 22፡13-20 መሠረት ወንድሞቻቸውን ከማጥፋታቸው በፊት ለምን ይህን ሊያደርጉ እንደወሰኑ ከእነርሱ አንደበት ለመስማት ፈለጉ (ጥበብ እና ብልሃት)። ከዚህ በፊት ጥቂቶች በሰሩት ሃጢአት እግዚአብሔር ህዝቡን ሁሉ በአንድ ዓይን አይቶ እንዴት እንደቀጣ በማስታወስ፥ የሰሩት ስራ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የተቀረውም የእስራኤል ህዝብ በእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ እንደሚገባ አስረዱአቸው።

**ኢያሱ 22፡21-31** ሁለት ከግማሽ የሆኑት ነገዶች "መሰዊያ" ሳይሆን "የመታሰቢያ ሐውልት" እንደሆነ የሰሩት እና ከእግዚአብሔር ውጭ ሌላውን ለማምለክም ሆነ እግዚአብሔርንም ራሱ ከሌላው የእስራኤል ህዝብ በተለየ ሁኔታ ለማምለክ እንደማይፈልጉ ቃል በመግባት አስረዱ። በዚህ ምክንያት ከመጥፋት ዳኑ።

**ኢያሱ 22፡32-34** እስራኤላዊያን ሁሉ በያሉበት በአንድ ልብ እግዚአብሔርን እያመለኩ ለመኖር ወሰኑ።

**ይህ ክፍል የሚያስተምረን ዋና ዋና ነገሮች፡-**

1. ህዝቡ መቼም ቢሆን የእርሱን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት ያሳያል። በማስተዋል እግዚአብሔርን መከተል/መኖር እጅግ

አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ የአዲስ ኪዳንም ጠንካራ ትምህርት እንደሆነ የማይካድ እውነት ነው።

2. ለህዝቡ ሁሉ ያለው አንድ እግዚአብሔር ነው። አንዱን እግዚአብሔር በተለያየ መሰዊያ አናመልከውም። አንድ መሰዊያ ብቻ ነው ያለው። ለእኛ አንድ ሊቀካህን፥ አንድ መሰዊያ፥ አንድ መስዋዕት ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ የሚያስተምር ሲመጣ ልንገስጽ ልንቃወምና ካልሰሙ ከህብረታችን እንኳ ልናስወግድ ዝግጁ መሆን አለብን። የጌታ ቃል በኤፌሶን መልዕክት “አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤6 ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ” ብሎ ይናገራል (ኤፌ 4:5-6)” ። በጠላት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ እርስ በእርሳችንም ከጥፋት ልንከላከል ያስፈልጋል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1) ኢያ 22:7-9 ስናነብ ኢያሱ ለሁለት ተኩል ነገድ የሰጣቸው መመሪያ ምንድ ነው?
2) ኢያ 22:10-11 መሠረት የተሠራው መሠዊያ አሥሩን የእስራኤልን ነገዶች ያስቆጣበት ምክንያት ምንድን ነው?
3) ኢያሱ 22፡12 “የእስራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ” የሚለው ሐረግና ቁ.14 የተዘረዘሩት ምን ያስተምረናል?
4) ኢያ 22:16-20 መሠረት የንግግራቸው ጭብጡ ምንድን ነው? ከዚህ በፊት የተሰሩትን ኃጢያቶችና ቅጣቱን መዘርዘራቸው ከአሁኑ ጋር የሚያገናኘው ምንድን ነው?

5) ከላይ በተነጋገርነው ታሪክ መሠረት የሌሎችን ሀሳብ ሳናውቅ ወደ ድምዳሜ መድረስ እንደሌለብን ምን እንማራለን?
6) ኢያሱ 22:18 አንድ ወገን በበደለው ሌላው ወገን በእግዚአብሔር የሚቀጣው ለምንድን ነው? ይህ ምን ሊያስተምረን ይገባል?
7) ኢያሱ 22: 21-34 ሁለት ከግማሽ የሆኑት ነገዶች ምስክር የሚሆን ሃውልት መፈለጋቸው ተገቢ ነው? ምን ጥንቃቄስ ያስፈልግ ነበር? ተወያዩ
8) ከዛሬ ታሪክ የተማርነውን ነገር እናካፍል?

**መደምደምያ**

ሁላችን የክርስቶስ አካል እንደመሆናችን፥ የአንዱ ኃጢአት ሌላውን አካል እንደሚጎዳ፥ የአንዱ በጎነት ለሌላው እንደሚተርፍ አውቀን፥ የወንድሜ ድካም ያገባኛል ብለን እርስ በእርሳችን ልንጸለያይ እና ልንገሣሠጽ ፈቃደኛ መሆን አለብን።

# ጥ ና ት አ ራ ት

# የ ም ን ባ ብ ክ ፍ ል፦ ኢ ያ ሱ 23፥1-16

# ርዕስ፦ ለ ዘ ላ ቂ ድ ል የ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ን ት ዕ ዛ ዝ አ ጥ ብ ቆ መ ያ ዝ

## የጥናቱ ዓላማ

የእስራኤል ሕዝብ በግልም ይሁን በማህበር በአንድ ልብ የእግዚአብሔርን ህግ በመጠበቅ ኃላፊነታቸውን ቢወጡ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንደሚዋጋላቸው በማስጠንቀቂያ የተነገራቸውን በማየት እኛም የሚጠበቅብንን በማድረግ በክርስትና ሕይወት በድል መኖር እንደምንችል ማስገንዘብ

## መግቢያ

ባለፈው ሳምንት ጥናት ኢያሱ ሕዝቡ እርሱ ከሞተ በኋላ በራሳቸው ቆመው እግዚአብሔርን እየታዘዙ መኖር መቻላቸውን ወይም አለመቻላቸውን ለማረጋገጥ እንደ ፈተናቸው፥ ፈተናውንም እንዳለፉ አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ በመካከላቸው የቀሩትን ከነዓናውያንን ጨርሰው ለማስወጣት እንዲጨክኑ ኢያሱ አደራ ሲሰጣቸው እናያለን። የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ባለመታዘዝ ስለሚገጥማቸው ጥፋት እየነገራቸው፥ እንዲሁም በመታዘዝ ስለሚገኘውም በረከት ስያረጋግጥላቸው እናያለን።

## የኢያሱ 23፥1-16 የታሪኩ ጭብጥ ሀሳብ

ይህ ምዕራፍ ሙሉ በሙሉ ኢያሱ የእያንዳንዱን ነገድ መሪዎች ስብስቦ ንግግር ያደረገበት ክፍል ነው።

**ኢያ 23:1-2** በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ኢያሱ የሚነግራቸው ነገሮች፥ በወቅቱ ችግር አይቶ ሳያሆን፥ ሁሉ ስላም በሆነበት ሰዓት ማስጠንቀቂያው ለእስራኤል ህዝብ ሁሉ ቢሆንም፥ መልዕክቱን

እንዲተገበር የሚረዱና የሚገሥጹ መሪዎች ስለሆኑና ስለሚያስፈልጉ፥ መሪዎች መጠራታቸውንም ይነግረናል።

**ኢያ 23:3-5** ጠላቶቻቸውን የወጋው ዋናው እግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል። ነገር ግን ይህ ማለት ኢያሱ አልተዋጋም ማለት አይደለም። ዋናው ተዋጊ እግዚአብሔር መሆኑን መንገሩ፥ ኢያሱ ሲሞት ተስፋ እንዳይቆርጡ በጥብቅ ለማሳሰብ ነው። ራሱ ኢያሱ መዋጋቱን መንገሩ ደግሞ፥ ተዋጊው እግዚአብሔር ነው ብለው እጃቸውን አጣምረው እንዳይቀመጡ፥ የእነርሱም ኃላፊነት እንዳለ እንዲያውቁ ነው።

**ኢያ 23:6-11** እግዚአብሔር ኢያሱን በኢያሱ 1፡7-8 ያዘዘውን ትዕዛዝ ኢያሱ ደግሞ ህዝቡን በዚህ ምዕራፍ ያዛል። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መስማትና መታዘዝ፥ ለመሪዎች የተሰጠ ብቻ ሳይሆን፥ ህዝቡ ሁሉ ሊያደርገው የሚገባ ነው።

**ኢያ 23:12-13** ይህ ክፍል ደግሞ የሚተርከው እግዚአብሔር ከነዓናውያንን ተዋግቶ ካስወጣላቸው በኋላ፥ አሁን ከቀሩት ከነዓናውያን ጋር በአንድነትና በኅብረት ለመኖር ስምምነት ቢያደርጉ፥ እግዚአብሔር ፍላጎታቸውን አክብሮ እንደሚተዋቸውና ከተዋቸው ግን እረፍት እንደሚነሱአቸው፥ መንፈሳዊ አይናቸውንም እንደሚያሳውሩ ያስጠነቅቃቸዋል።

**ኢያ 23:14-16** እግዚአብሔር የገባው የበረከት ቃል ለመጠበቅ የሚተጋ አምላክ ብቻ ሳይሆን፥ ቃል ኪዳኑን በሚያፈርሱት ላይ ደግሞ የገባውን የፍርድ ቃል እስከ መጨረሻው ድረስ የሚጠብቅ አምላክ መሆኑ እንዳይዘነጉ ያሳታውሳቸዋል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ኢያ 23:1-3 በማንበብ ከክፍሉ ምን ተረዳችሁ?
2. ኢያ 23፥4-5 መሠረት ያልተወረሰውን የከነዓንን ምድር ለመውረስ እርግጠኛ ሊያደርጋቸው የሚችለው ነገር ምንድ ነው ትላላችሁ?
3. ኢያ 22: 6-11 ኢያሱ ለሕዝቡ የሰጠው የአድረጉ ትዕዛዝና ማሳሰቢያ በዝርዝር ተነጋገሩበት? ከኢያሱ የአገልግሎት ጅማሬ ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ተወያዩ (ኢያሱ 1:7-8)?
4. በኢያሱ 23:12-16 ኢያሱ የሰጣቸው የአታድርጉ ማስጠንቀቂያና ምክር ምንድ ነው? ባይታዘዙስ ውጤቱ ምን ይሆናል? ለምን?
5. ከዛሬው ጥናታችን ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳንል በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ጸንቶ በመቆም እየታዘዙ ስለ መኖር ምን ተማርን?
6. ኢያሱ 23፥11 "አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትወድዱት ዘንድ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ" ማለቱ ካልተጠነቀቅን የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኛ ልብ ሊርቅ እንደሚችል ያሳያል ማለት ነው?

**መደምደምያ**

መሪዎች ይመጣሉ ይሄዳሉ። እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ ይኖራል። እግዚአብሔር መሪዎችን እንደረዳ፥ ሕዝቡንም ሁሌ ይረዳል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ላይ ተደግፎ መሪዎች ኖሩም አልኖሩም የተሰጠንን ኃላፊነት መወጣት አለብን።

# ጥናት አምስት

## ርዕስ፡ ቃል ኪዳንን እንደገና ማደስ

## የምንባብ ክፍል፡ ኢያሱ 24፡1-33

**የጥናቱ ዓላማ**

ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳኑን እንደገና እንዳደሰ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን አደራ ለመወጣት ከእርሱ ጋር የገባነውን ቃል ሁልጊዜ ኪዳን ቆም ብሎ ማደስ እንደሚያስፈልግ ለማስረዳት።

**መግቢያ**

ባለፈው ጥናት ኢያሱ ለሕዝቡና ለመሪዎቹ የሰጠውን ትዕዛዝ እና አደራ አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ በኢያሱ 23 የሰጣቸውን ትዕዛዙን ለመጠበቅ፥ ለአደራው ታማኝ ለመሆን እንዲችሉ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳናቸውን ሲያድስ እናያለን። **በኢያሱ 24:1-11** ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ ከአብርሃም ጀምሮ እንዴት እንዳበዛቸው፣ከግብጽ ባርነት እንዴት እንዳወጣቸው፣በምድረ በዳ እንዴት እንደመራቸው እና የከነዓንን ምድር እንዴት እንዳስወረሳቸው የሚናገር ሲሆን **ኢያሱ 24:12-15** ደግሞ ሕዝቡ በፈቃዳቸው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያሳስባቸዋል፤በመቀጠልም ከቁ.16-18 የሕዝቡን በፈቃቸው ላይ የተመሠረተ እግዚአብሔርን የማምለክ ቃል ኪዳን እናያለን (ማለትም ከእግዚአብሔር ሌላ ጣኦትን ላለማምለክ ቃል ገቡ)። **ኢያሱ 24:19-25** የእግዚአብሔርን ቅድስና እና የሕዝቡን በድጋሚ በፈቃዳቸው ቃላቸውን ማጽደቃቸውን ራሳቸው ሕዝቡ ምስክሮች እንደሆኑ ይናገራል። **ከቁ.26-27** ለቃል ኪዳናቸው የምስክር ድንጋይ በተጨማሪ ይተክላል። በመጨረሻም **ኢያሱ 24:28-33** የኢያሱንና የካህኑን የአልዓዛር መሞት

እና ከእነርሱ ቀጥይ የነበረው ትውልድ ለእግዚአብሔር መታዘዙን ያሳያል። ይህ ክፍል ከመሳ 2:6-8 ተመሳሳይነት ያለውን ታሪክ እናያለን።

## የኢያሱ 24፡1-33 የታሪኩ ጭብጥ ሀሳብ

**ኢያሱ 24:1** የእግዚአብሔር የመገናኛው ድንኳን ያረፈበት አዲሱ ቦታ ሴኬም ነው። ሕዝቡንና መሪዎቹን በመገናኛው ፊት ማቆሙ በእግዚአብሔር ፊት ማቆም ነው። በእግዚአብሔር ፊት ማቆም ደግሞ ያስፈለገው፥ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳናቸውን ሊያድሱ ስለሆነ ነው። በሲና ተራራ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ቃል ኪዳን እንደ ገቡ፥ አሁንም በመገናኛው ድንኳን ፊት ቆመው ቃል ኪዳናቸውን ያድሳሉ።

**ቁጥር 2-13** በእነዚህ ቁጥሮች ኢያሱ የእስራኤልን ታሪክ በአጭሩ ጠቅልሎ ያስታውሳቸዋል። አባቶታቸው ሌሎችን አማልክት ከሚያመልኩበት ቦታ አብርሃምን እንደመረጠውና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፥ በግብጽ በምድረበዳ እንዲሁም በከንዓን ምድር እንዴት እንደመራቸው ያስታውሳቸዋል።

**ኢያሱ 24:14-15** ታሪካቸውን ካስታወሳቸው በኋላ፥ ዛሬም ውሳኔ እንዲወስኑ ይነግራቸዋል። ድሮ አባቶቻቸው ወደአመለኩአቸው አማልክቶች እንዳይመለሱ ቢመክርም፥ ወይ አማልክቱን ወይ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዲመርጡ ነጻነት ግን ይሰጣቸዋል።

**ኢያሱ 24:16-18** ለኢያሱ ምክር የእስራኤል ልጆች ሲመልሱ፥ እግዚአብሔርን ዛሬም ለማምለክ እንደወሰኑ ይነግሩታል። ምክንያታቸውን ሲነግሩት ግን እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ስላደረገላቸው፥ ስላዳናቸው ብቻ ነበር። ይህ በራሱ ችግር ባይኖረውም፥

ብቻውን ግን በቂ አይደለም። ከዚህም የተነሳ በቁጥር 19 ላይ ኢያሱ ሕዝቡን እግዚአብሔርን ማምለክ እንደማይችሉ ይነግራቸዋል። የማይችሉበት ምክንያት ሲነግራቸው "ቅዱስ ነውና" ይላቸዋል። ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው። እግዚአብሔር ከሌሎች አማልክት ሁሉ በላይ ሊመለክ የሚገባው፥ ስላደረገው የማዳን ሥራ ብቻ ሳይሆን የተቀደሰ ወይም የተለየ አምላክ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ሲገቡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቀድሰዋል፥ እግዚአብሔርንም ለእነርሱ "ቀድሰውታል" ወይም "ለይተውታል።" ስለዚህ ወደሌላ ሲሄዱ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው። ቀናተኛ የሆነው በቃል ኪዳን አብረው ለመኖር የተሳሰሩ ስለሆነ ነው። በቁጥር 20 ደግሞ ቅንአቱ ወደ ቅጣት እንደሚወስደው ይናገራል። አውቆ ቃል ኪዳኑን የሚያፈርሰው ሰው እግዚአብሔር ይቅር እንደማይለው ይናገራል።

**ቁጥር 21-23** ሕዝቡ ደጋግሞ ቃል ኪዳኑን እንደሚጠብቅ፥ እግዚአብሔርን ብቻ እንደሚያመልክ ቃል ይገባል። ከ21-28 እንደምናየው ኢያሱም ለገቡት ቃል ኪዳን ምስክር ራሳቸውና ቃል ኪዳኑ የተጻፈበት ሀውልት/ድንጋይ እንደሆኑ ይነግራቸዋል።

**ኢያሱ 24፡29-33** በኢያሱንና አብረውት ይመሩ በነበሩ ሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ለገቡት ቃል ኪዳን እስራኤል ሁሉ ታማኝ ሆነው እንደኖሩ ይነግረናል። ይህ የሚያሳየው መሪ ምን ያህል ወሳኝ መሆኑን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ኢያሱና ሽማግሌዎቹ ከሞቱ በኋላ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል በጥቂቱም ቢሆን ይጠቁማል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢያ 24:1-11 ኢያሱ ለሕዝቡና ለመሪዎቹ የነገራቸውን ነገር አካፍሉ?
2. በኢያ 24:2-15 ክፍል የተተረከው የእግዚአብሔርንና የእስራኤል ታሪክ ማወቅ በወቅቱ ለሚሰሙ ሰዎች ቃል ኪዳኑን ለማደስ ለምን እንደሚጠቅም ተወያዩ?
3. ኢያ 24:16-18 መሠረት የሕዝቡ ምላሽ ምን ነበር? የእነርሱ ምላሽ ለወደፊት ኑሮአቸው ለምን አስፈለገ?
4. በኢያ 24:19-20 ኢያሱ ለሕዝቡ በምን ሁኔታ ሲሆኑ ነው እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም የሚላቸው?
5. ኢያ 24፡21-24 በኢያሱና በሕዝቡ መካከል የደረሱበትን ስምምነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?
6. በኢያ 24:25-27 ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳንን ማደሱን ተከትሎ ኢያሱ ያደረገው ምንድ ነው? ለምን?
7. ከኢያ 24:28-33 ባለው ክፍል የተከናወኑ ዋና ዋና ነገሮች ምን ምንድ ናቸው? የኢያሱ ማስጠንቀቂያና ምክርስ ትውልዱን ምን ያህል አስጉዞታል?
8. ከዛሬው ጥናት ከጌታ ጋር ያለንን ህብረት በጥንቃቄ እየመረመረን ስለመዳዝ የተረዳችሁትን አካፍሉ?

## መደምደምያ

ዓለም ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ሕዝብም ሁሉ ባይከተለው እንኳ እኛ በግልና በቤተሰባችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቃል ኪዳን አጥብቀን ልንይዝና ሁሌም ልናድስ ይገባናል።

# ጥናት ስድስት
# ሥራው ይቀጥላል
# የምንባቡ ክፍል፡ መሳፍንት 1:1-19

**የጥናት ዓላማ፡-**

የእግዚአብሔርን ሥራ ለማስቀጠል ሁል ጊዜ አብሮነርቱን መሻት አስፈላጊ መሆኑን በማስገንዘብ ፡ እኛም በዘመናችን የእግዚአብሔር ሥራ እንዲቅጠል የእግዚአብሔርን አብሮነት በመፈለገ እንድንበረታ ለማሳሰብ

**መግቢያ፡-**

ይህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ እና የመፈለግ ውጤት **(መሳ 1:1-20)** ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ፈጽማችሁ አስወግዱ የተባሉትን ነገር ያለማስወገድ ችግር ታሪክ ነው **(መሳ 1:21-36)**። በዚህ ጥናት የመጀመሪያውን ክፍል እናጠናለን።

በኢያሱ መጽሐፍ እንደምናየው እስራኤላውንያን ከነዓንን ለመውረስ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ፍላጎት ነበራቸው፥ መልካም ጅማሬም ነበራቸው። ኢያሱ ከሞተ በኋላ ግን ይህ ፍላጎትና የመታዘዝ ቆራጥነት አልታየባቸውም። ይልቁንም ከከነዓናውያን ጋር አብረው ለመኖር ጽኑ ፍላጎት አሳዩ። ይህም አለመታዘዝ ሁሉም ነገዶች ያሳዩት ችግር እንደነበር እናያለን። ይህም አለመታዘዝ እነርሱን እራሳቸውን በምድሪቱ ላይ ያላቸውን ባለቤትነት ማሳጣት እንደጀመረ ይህ ክፍል ያሳየናል።

## የዚህ ክፍል ታሪክ አጭር ማብራሪያ (መሳ 1:1-19)

**መሳ 1፡1** የኢያሱ መሞት የሚያሳየን እስራኤል ወሳኝ የለውጥ ጊዜ ላይ እንዳለች ነው። የኢያሱ ሞት በዙርያቸው ያሉ አሕዛቦችን

የሚያስደስትና እስራኤልን ለመውጋት ድፍረት የሚሰጥም ነው። ምን አልባትም በቁጥር1 እየጻለዩበት ያለው ውጊያ የኢያሱን ሞት አይተው እስራኤልን ሊወጉ የተዘጋጁትን የከነዓናውያንና የፌሪዛውያንን ሕዝቦች በተመለከተ ይሆናል። የመሪ አለመኖር ሕዝቡን በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ ሊያስደፍር ሊያስንቅ ይችላል። ይህ ምዕራፍ እያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ የእግዚአብሔርን ግልጽ ትዕዛዝ ባለመታዘዝ እንዴት እንደወደቀ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ሁሉንም ነገዶች ተራ በተራ ይገልጻል።

**መሳ 1፡2-7 17-19** የይሁዳንና የስምኦንን ድካም የሚያሳይ ነው። በዋነኝነት ግን የይሁዳን ድካም ያሳያል። ይሁዳ ለእርሱ በተሰጠው ሃላፊነት ስምኦንን መጋበዙ ፍርሃቱን የሚጠቁም ነው። ችግሩ እዚህ ጋር ቢጀምርም በዋነኝነት ግን የሚታየው አዶኒቤዜቅን በሕይወት እንዲኖር መፍቀዳቸው ነው። አንዳንድ አሕዛቦችን በድፍረት ቢዋጉም፥ አንዳንዶችን ግን ካላቸው መሳሪያ የተነሳ ፈርተው አልተዋጉአቸውም። የእግዚአብሔር መገኘት አብሮአቸው እንደሆነ ቢያውቁም፥ ለመታዘዝ ግን አልጨከኑም።

የይሁዳን ድካም የሚያጎላው በቁጥር 8-16 የእነርሱ አባቶች የካሌብንና የጎቶንያልን ፍጹም መታዘዝ ነው። ሁለቱም ለእግዚአብሔር ፍጹም የታዘዙ ነበሩ። ይሁዳ ግን ከአባቶቹ አልተማረም።

## የውይይት ጥያቄዎች፡-

1. በመግቢያው መሠረት ምዕራፉ የተከፈለባቸው ሁለት ዋና ሀሳቦች ምንድ ናቸው?
2. መሳ 1፡1-2 ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

3. መሳ 1:3 ከነዓናውያንን ለመውጋት ከመውጣቻው በፊት የይሁዳ ሰዎች ምን አደረጉ? ከቁ.17-18 ካለው ታሪክ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
4. መሳፍንት 1:4-11 ክፍል የተከናወነውን አብራሩ?
5. በመሳፍንት 1:12-15 መሠረት ካሌብ ቅርያት ሤፍርን ለማያዝ የተጠቀመበት መንገድ ምንድ ነው?
6. በዚህ ክፍል መሠረት "በእግራችሁ የረገጣችሁን ቦታ ትወስርሳላችሁ" የተባለው ተስፋ እያለ የእነርሱ መዋጋት ለምን አስፈለገ? ከዚህ እኛስ ምን እንማራለን?
7. ለስኬታቸው ዋና ምክንያት ምንድ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለእኛስ ምን ያስተምረናል?

**መደምደሚያ፡-**

ለሁለንተና ድል ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔር አብሮነት መሠረታዊ ነገር ነው። ለዚህም የእኛ መታዘዝና እርሱን መፈለግ ወሳኝ ነገር ነው።

# ጥናት ሰባት
# እግዚአብሔር ሥራውን ይቀጥላል
## የምንባብ ክፍል፡- መሳፍንት 1:19-36

**ዓላማ፡-**

የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእርሱ ያለመታዝዝ የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚገባ እንዳይቀጥል የሚያሳድረውን ተጸዕኖ በማስገንዘብ፡ እኛም በተተኪው ትውልድ የእግዚአብሔር ሥራ ለማቀጠል በመታዘዝ ህይወት መኖር እንደሚያስፈልገን ለማስገንዘብ ነው

**መግቢያ**

በዚህ ጥናት **የመሳፍንትን 1:19-33** ያለውን ታሪክ እናያለን። የዚህ ምዕራፍ ዋናዎቹን ሁለት ነገሮች እንደሚከተለው ነው። በዚህም ዕራፍ ሀለተኛ ክፍል ደግሞ ፈጽማችሁ አስወግዱ የተባሉትን ነገር ያለማስወገድ ችግር ታሪክ **(መሳ 1:21-36**) ነው። በዘዳግም 4:37-38፣ መሳ 20:16-18፣ ዘጸ 23:33 እንደሚለን በጣኦት አምልኮ እንዳያጠምዷቸው ፈጽመው እንዲያጠፉ ተነግሯቸው ነበር።

በኢያሱ መጽሐፍ እንደምናየው እስራኤላውንያን ከነዓንን ለመውረስ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ፍላጎት ነበራቸው፥ መልካም ጅማሬም ነበራቸው። ኢያሱ ከሞተ በኋላ ግን ይህ ፍላጎትና የመታዘዝ ቆራጥነት አልታየባቸውም። ይልቁንም ከከነዓናውያን ጋር አብረው ለመኖር ጽኑ ፍላጎት አሳዩ። ይህም አለመታዘዝ ሁሉም ነገዶች ያሳዩት ችግር እንደነበር እናያለን። ይህም አለመታዘዝ እነርሱን እራሳቸውን በምድሪቱ ላይ ያላቸውን ባለቤትነት ማሳጣት እንደጀመረ ይህ ክፍል ያሳየናል።

**የክፍሉ አጭር ማብራሪያ (መሳ 1:19-36)**

**መሳ 1፡19-36** እንደምናየው የሌሎቹም ነገዶች ጥፋት አሕዛብን ከማጥፋት ይልቅ፥ አብረዋቸው ለመኖር መፈላጋቸው ነው። ይህም ፍላጎት በይደር ያመጣባቸውን ችግር ይህ ክፍል ይገልጣል። ቁጥር 21 ብንያም በእርሱ ክልል የነበሩትን አላወጣቸውም። ቁጥር 27 ምናሴም አላወጣቸውም፥ ነገር ግን በዚህ ቁጥር እንደምናየው ከነዓናውያን "በዚያ አገር በመቀመጥ ጸኑ" ። ይህ የሚያሳየው ቀስ እያሉ ከነዓናውያን ጉልበት እያገኙ መሆኑን ነው። ቁጥር 28 የሚነገረን እስራኤል እንደ አገር ከነዓናውያንን ከምድሪቱ ማውጣት የሚያስችል ብርታት ቢኖራቸውም፥ ፈጽመው ግን አላወጡአቸውም። ቁጥር 29 ከነዓናውያን በእስራኤል ልጆች መካከል ቢቀመጡም በቁጥር 32 ግን የእስራኤል ልጆች በከነዓናውያን መካከል ተቀመጡ። ቁጥር 32 የሚነግረን አሁን ከነዓናውያን በምድሪቱ ባለቤት እንደሆኑ ነው። ቁጥር 34 ደግሞ የእስራኤል አንዱ ነገድ ከተቀበለው ምድር እንዲወጣ ተደረገ። ስለዚህ መጨረሻው ከምድሪቱ መውጣት ሆነ።

በተጨማሪ ለማጠናገር ይህ ክፍል የሚያሳየው፥ እግዚአብሔር የሰጣቸው ትዕዛዝ ባለመታዘዝ፥ በእነርሱ ዓይን መልካም የመሰላቸውን በማድረግ ማለትም ከነዓናውያንን ከምድሪቱ ከማስወጣት ይልቅ አብረዋቸው ለመኖር በመወሰናቸው፥ በመጨረሻው ይህ የራሳቸው ውሳኔ እራሱ ከምድሪቱ እንዲወጡ አደረጋቸው። ይሁዳ ከሌሎቹ ነገዶች ይልቅ በአንዳንድ አሕዛቦች ላይ ድል የተቀዳጀ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ልክ እንደሌሎቹ ነገዶች ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሰ ነው የሚታየው። እግዚአብሔር ትክክል ነህ ወይም አይደለህም የሚለው ከሌሎች ጋር አነጻጽሮ ሳይሆን፥ ከሰጠው ትዕዛዝ አንጻር ብቻ ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. መሳ 1፡19-21 መሠረት በምድሪቷ የነበሩትን ሰዎች ማስወጣት ያልቻሉት ለምንድ ነው?
2. መሳ 1፡22-26 የዮሴፍ ልጆች ሎዛን የማሸነፍ ወይም ድል የማድረግ ምስጥሩ ምንድ ነበር? ይህን ክፍል ከጥያቄ አንድ ጋር አነጻጽሩ።
3. በመሳ 1:27-36 ክፍል ለሁሉም ነገዶች የተነገረው ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ ምን ነበር?
4. በመሳ 1፡33 መሠረት ከሰዎቹ ጋር አብረው ለመኖር የተውበት ምክንያት ምንድ ነው?
5. ማስወጣት ያልቻሏቸው ህዝብ የመሳሪያና የውጊያ ስልት ብልጫ ስላላቸው ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?
6. በዚህ ክፍል ታሪክ መሠረት የሽንፈታቸው ምክንያት ምን ነበር?
7. በዛሬ ጥናት ያለመታዘዝ ህይወት ለውድቀት እንደሚዳርገን የተረዳችሁትን አካፍሉ?
8. በዛሬው ጥናት መሠረት በህይወታቸን የጎደለብንን እያሰብን እንጸልያለን።

**መደምደሚያ፡-**

ጌታ አጥፉ ወይም ተው ያለንን ነገሮች ጨርሰን ማጥፋት ወይም መተው መቻል አለብን። ለአማኞች ከላስፈላጊ ነገሮች ጋር አብሮ መኖር ወጥመድ እንደሚሆንብን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

# ጥናት ስምንት

## የንባብ ክፍል መሳ 2:1-9

## እግዚአብሔርን ከመከተል መተው ጉዳት አለው!

**ዓላማ፡-**ለእስራኤላውያን ሽንፈት ምክንያት የሆነውን ዋና ጉዳይ በመሳየት፤ ዛሬ በግል ሕይወታችንም ቢሆን በህብረታችን፤ ድል ባጣንባቸው ጉዳዮች፤ እራሳችንን መመርመርና ተገቢውን እርምጃ እንድንወስድ ማስገንዘብ።

**መግቢያ፡-**እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የማላት ምድር ለመውረስ፤ እስራኤላውያን ከጠላቶቻቸው ጋር መዋጋት ነበረባቸው።ይህንን ሀሳብ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ብለናል። ይህ ማለት ግን የእነርሱ ውጊያ ብቻውን ያወርሳቸዋል ማለት አልነበረም። ከሚታየው ሥጋዊ ውጊያ ጀርባ ያለው መንፈሳዊ ውጊያ ነበር፤ ያም የድላቸው ዋናው ምክንያት ነበር። ጠላቶቻቸው ይሸነፉ የነበረውም ከእነርሱ ያነሰ ሰራዊትና የውጊያ ስልት ስለ ነበራቸው ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ስለ ነበረ ነበር። በመሳፍንት 2:1-5 ተጽፎ እንደምናነበው፤ እግዚአብሔር መዋጋቱን ሲያቆም፤ ሕዝቡ እንደ ማንም ተራ ሕዝብ ሆኖ በጠላቶቹ ሲሸነፍ ሲማረክና ሲገብር ይታያል።

ሕዝቡ ፊቱን ከአምላኩ ሲመልስ ማለትም ወደ ተለያዩ ጣኦታት ሲዞር (ዘዳግም፣ ቀጣይ ደሎችን ከማየት ይታገዳል። ሁሌ ያለፈውን ፣ የትላቱን ብቻ የሚናገር ፤ ትዝታ ደርዳር ይሆናል። በቀደመው ድል የኖረው ትውልድ ያልፍና፤ ድሉንም ድል ሰጭ አምላክ የማያውቅ ትውልድ ይፈጠራል። ይህ ደግሞ አሳዛኝ ውድቀት ነው። ከምዕራፍ ሁለት ቁጥር አስር ጅምሮ የምናነበው ታሪክ የዚህ እውነታ ማስረጃ ነው።

ጌታን አምኖ ለእርሱ በመታዘዝ መኖር ዋናው በመንፈሳዊ ህይወታችን በድል የመኖር ምክንያት ነው።

**የመሳፍንት 2:1-9 ጭብጥ ነገር በአጭሩ**

**መሳ 2:1-3** የእግዚአብሔር መልዓክ ለህዝቡ ህጉን ሰበከ/ህ አጠናከረ-ህጉ ሙሴ ወይም ኢያሱ ያስተላለፉት ነገር ብቻ እንዳልሆነ ይህ ክፍል ያስተምረናል። በዚህ ክፍል የተገለጠው መልዓክ ብቻ ሳይሆን መልዓኩ ራሱ እግዚአብሔር እንደተገለጠም ይታመናል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱ በተለያዩ ቦታዎች እንደ ገለጠ የተረጋገጠ እውነት ነው።

**መሳ 2:4-6** እግዚአብሔር ለወቀሳቸው ነገር ህዝቡ በለቅሶ የንስሃ ምላሽ እንደሰጡ ይናገራል። ለቅሶአቸው መስዋዕትን በማቅረብ መተግበሩን ታሪኩ ይነግረናል። ይግህም በጊዜው በትክክል መመለሳቸውን ያሳያል።

**መሳ 2:7-9** ኢያሱ በነበረበት ዘመን ሽማግሌዎችም ይሁን ህዝቡ ሁሉም ባይሆኑም እግዚአብሔርን አምልከው እድሜያቸውን እንደጨረሱ ይነግረናል። በተጨማሪም ይህ ክፍል ልክ እንደሙሴ የኢያሱንም ሞት ይተርካል። ማንም አገልጋይ ምንም ጥሩ ነገርም ቢሰራ ይህ ምድር ለእርሱ እንግዳ እንደሆነ መወቅ አለበት። እንደ ጌታ ፈቃድ ህዝቡን መምራቱን ብቻ መፈተሽ ነው የሚያስፈልገው። መጽሐፉ ኢያሱን “የእግዚአብሔር ባሪያ” ብሎ በእድሜው መጨረሻ ይደመድማል። የእግዚአብሔር ወይም የጌታ ባሪያ በአዲስ ኪዳንም ትልቅ ትርጉም ያለው የአገልጋዮች መጠርያ ነው።

በማቴዎስ ወንጌል በተራራው ስብከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን ትምህርት ለእግዚአብሔር ህግጋት ስለመኖር ነው (ማቴ

ከምዕራፍ 5-7)። እንዲሁም የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች ሁለተኛው ክፍሎች (ለምሳሌ ኤፌ 1-3 ክፍል 1 ሲሆን ከ4-6 ክፍል 2 ነው) በተማርነው ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚገባ እንድንኖር በጥብቅ ይነግረናል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. መሳ 2:1-3 መልአኩ አስቀድሞ ስለተሰጣቸው ኪዳን ያስታወሳቸው ለምን ነበር? ሕዝቡስ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደነበረ ተወያዩ ? ዘዳ 7:2-4 ይነበብ።
2. እስራኤላውያን በቃል-ኪዳኑ ያልጸኑበት ምክንያት ለምን ነበር?
3. ቃልኪዳኑን ባለመጠበቃቸው ምክንያት የደረሰባቸው ችግር ምን ነበር?
4. በመሳ 2:4-5 መሰረት፤ የመልአኩን ቃል ከሰሙ በኋላ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?
5. ከመሳ 2:7-9 በማንበብ ከኢያሱ የህይወት ፍጻሜ ምን እንማራለን?
6. ከዛሬው ጥናት ድል ያጣንባቸው ጉዳዮች ቢኖሩ ልንወስደው ስለሚገባን እርምጃ ምን ተማርን?
7. በዛሬ ጥናት ሃሳብ መሠረት በአሸናፊነት ህይወት መኖር እንድንችል በጋራ እንጸልይ።

***መደምደምያ፡-***

እግዚአብሔር የእርሱን ትዕዛዝ እንድንጠብቅ ይጠብቅብናል። የእግዚአብሔርን ትእዛዙን አለመጠበቅ የውድቀት ውጤት ያመጣል ። ይህ ምድር ዘላለማዊ ቤት አይደለም። የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው።

# ጥናት ዘጠኝ

## የንባብ ክፍል መሳ 2:10-3:6

## እግዚብሔርን የማያውቅ ትውልድ!

**ዓላማ፡**

እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ ያለውን የእልህኝነት ኑሮው ያስከተለበትን የሽንፈት ሕይወት በማሳየት፤ ዛሬ እኛም እንደ እነርሱ እግዚአብሔርን አስቆጥተን በእልከኝነት እንዳንመላለስ እና ውጤቱንም እንዳናጭድ ጥበብ እንዲበዛልን ማሳሰብ

**መግቢያ**

ባለፈው ጥናት እያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ከነዓናውያንን እንዲያጠፉ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዝ እንዳልጠበቁ አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ የምናየው እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ይህንን አለመታዘዛቸውን እንደገሰጸ፥ እስራኤላውያን ግን ተግሳጹን ሰምተው ከነዓናውያንን ከማጥፋት ይልቅ፥ ለተግሣጹ የሰጡት ምላሽ ልቅሶ ብቻ እንደነበር፥ አለመመለሳቸውንም አይቶ እግዚአብሔር እንዴት እንደቀጣቸው እናያለን።

**መሳፍንት 2:10-15** ይህ ክፍል እንደሚነግረን አዲሱ ትውልድ በእግዚአብሔርና በኢያሱ ፊት የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተው የአህዛብን የኑሮ እና የአምልኮ ዘይቤ ስለተከተሉ እግዚአብሔር ለጥፋት አሳልፎ ሰጣቸው። ይህም ደግሞ ለእነርሱ እጅግ ከባድ እንደነበረ ያስረዳል። ጥቅሱም እንደሚከተለው ይላል

“ያ ሁሉ ትውልድ ወደ አባቶቹ ከተከማቸ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ

ትውልድ ተነሣ። 11 ከዚያም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረጉ፤ የበኣል አማልክትንም አመለኩ። 12ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉ፤ በዙሪያቸው ያሉት ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን አማልክት ተከተሉ፤ ሰገዱላቸውም። እግዚአብሔርንም አስቈጡት፤ 13እርሱን ትተው በኣልንና አስታሮትን አምልከዋልና 14 እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በመቈጣቱ ለሚዘርፏቸው አሳልፎ ሰጣቸው፤ በዙርያቸው ላሉ ጠላቶቻቸው ሸጣቸው። 15 እስራኤላውያን ለውጊያ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረውና እንደ ማለው ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ ትከፋባቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ እጅግ ተጨነቁ"(መሳ 2:10-15)።

**መሳ 2፡16-3:6** ባለው ክፍል አንደኛ የእስራኤል ህዝብ ውድቀት በሰው ፊት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ነበር፡ይላል። አንዳንድ ጊዜ ህይወት ከውጪ በሰው ፊት ሲታይ ትክክልና ኃይማኖት መልክ ያለው ሊመስል ይችላል  ነገር ግን የሚመዘነው በእግዚአብሔር ፊት ነው። በዚህ ክፍል ሁለተኛው ነገር ከኢያሱ በኋላ በነበረው ትውልድ እግዚአብሔርም ሊፈትናቸው አህዛብን ሙሉ በሙሉ በራሳቸው በእስራኤላዊያን አለመታዘዝ ምክንያት አላስወጣቸውም። የቀሩትም አህዛብ ለእነርሱ ውጥመድ ነበሩ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ደግሞ ጦርነት ህዝቡ ጦርነት እንዲማሩ ነው ይላል (መሳ 3:1-6)።

**የመሳፍንት 2:10-3:6  አጭር ማብራሪያ**

**መሳ 2:1-5** እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከዚህ በፊት የተናገራቸውን ነገር ያስታውሳቸዋል። ይህም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር

የገባውን ቃል ኪዳን ሊጠብቅ ቃል መግባቱን እና እነርሱም እንዲጠብቁ እንዳዘዛቸው አስታውሶ፥ እነርሱ ግን ከእርሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው ከከነዓናውያን ጋር ሌላ ቃል ኪዳን ገቡ። ስለዚህ ቃል ኪዳን የገቡላቸው ከነዓናዊያን እንደሚያስጨንቁአቸው እና የከነዓናዊያንን አማልክቶች ደግሞ ወጥመድ እንደሚሆኑባቸው ይነግራቸዋል። ይህን የተናገረበት ምክንያት ለእስራኤል እንደገና የመመለስ እድል ለመስጠት ነበር። እነርሱ ግን ከነዓናውያን ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ከማፍረስና እነርሱን ከማጥፋት ይልቅ ምላሻቸው ለቅሶ ብቻ ነበር። ንስሃ መመለስ እንጂ ማልቀስ ወይም እያለቀሱ መናዘዝ አይደለም።

**መሳ 2፡6-10** የቀደመው ትውልድ እግዚአብሔር በኢያሱ በኩል ያስተላለፈላቸውን መልዕክት ተግብረው እግዚአብሔርን አምልከው አለፉ። የቀደመው ትውልድ ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ ተነሣ። ይህ ማለት ምንም አልሰሙም ማለት ሳይሆን፥ ለሰሙት እውነት እውቅና አለሰጡም ማለት ነው።

**መሳ 2፡11-15** የእስራኤል ልጆች በኣልና አስታሮት የተባሉትን የከነዓናውያንን አማልክትን አመልኩ። ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ቁጣ ስለነደደ፥ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው፥ ጠላቶቻቸውም አስጨነቁአቸው፥ በሁሉም አቅጣጫ የእግዚአብሔር እጅ ከፋችባቸው።

**መሳ 2፡16-19** እግዚአብሔር መሓሪ ስለሆነ መጨነቃቸውን አይቶ፥ ከጠላቶቻቸው የሚያድኑአቸውን መሳፍንትን አስነሳላቸው። የእግዚአብሔርም ምህረት ወደ ንስሃ አላመጣቸውም። ነገር ግን አብዝተው የአሕዛብ አማልክትን ማምለክ ቀጠሉ። እግዚአብሔርም እንደገና ይቀጣቸው ነበር። እነርሱም ጭንቀቱ ሲበዛባቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሁ ስለነበር መሳፍንትን እያስነሳ ይታደጋቸው ነበር።

እያንዳንዱ መስፍን ከሞተ በኋላ ተመልሰው በኃጢያታቸው ይቀጥሉ ነበር። በመሳፍንት ዘመን ሁሉ እስራኤል በዚህ አዙሪት ውስጥ ነበሩ።

**መሳ 2፡20-23** ይህ ክፍል የሚነግረን እግዚአብሔር ከቁጣው የተነሳ የተናገረውንና የወሰነውን ውሳኔ ነው። ይህ ክፍል እግዚአብሔር መሳፍንትን ሲያስነሳ ለምን ከነዓናውያንን እንዲያጠፉና ከመካከላቸው እንዲወጡ እንዳላደረገ የሚያስረዳ ክፍል ነው። በፊት በመካከላቸው እንዲሆኑ የተወበት ምክንያት እነርሱን ለመፈተን ነበር። እነርሱም ፈተናውን ወደቁ። ከእስራኤል ኃጢያት የተነሳ እግዚአብሔር ከነዓናውያንን ከመካከላቸው መቼም ቢሆን ላያወጣ መወሰኑን ይናገራል።

**መሳ 3፡1-6** ይህ ክፍል በድጋሚ የሚነግረን እግዚአብሔር ለምን የተወሰኑ ከነዓናውያንን በምድሪቱ እንዳስቀረ ነው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገበት ምክንያት አዲሱ ትውልድ በሙሴ በኩል እስራኤል ከነዓናውያንን እንዲያጠፉት ያዘዘውን ትዕዛዝ ይታዘዙ ወይም አይታዘዙ እንደሆን ለማወቅ ነው። እነርሱ ግን ከማጥፋት ይልቅ ከከነዓናውያን ከኬጢያውያንም ከአሞራውያንም ከፌርዛውያንም ከኤዊያውያንም ከኢያቡሳውያንም ጋር አብረው ኖሩ፥ በጋብቻ ተሳሰሩ፥ አማልክቶቻቸውን አመለኩ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመሳ 2:11-15 መሠረት ከኢያሱ በኋላ የተተካው ትውልድ የፈጸሙት ያለመታዘዝ ዝርዝር ምን ምን ነበር?
2. መሳ 2:11ና 3:7፣ ስናነብ ምን ያስተምረናል? ለተጨማሪ ማብራሪያ የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ እንችላለን (4:1, 6:1፣ 10:6፣ 13:1)፡፡

3. በመሳ 2:10-13 መሠረት የኋለኛው ትውልድ እግዚአብሔርን ያለማወቃቸው መለኪያው ምንድ ነው?
4. በዚያ ክፉ ትውልድ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ የተገለጠው እንዴት ነበር? በዝርዝር ተነጋገሩበት።
5. መሳ 2፡16-18 መሰረት የሚገባቸው ሳይሆን እግዚአብሔር መስፍን ወይንም ታዳጊ ያስነሳቸላው ምክንያት ምን ነበር? መሳ 2:1ን ማመሳከር እንችላለን?
6. መሳ 2: 19-20 መስፍኑ ከሞተ በኋላ የህዝቡ ህይወት የባሰ የተወሳሰበት ምክንያት ለምንድ ነው?
7. መሳ 2: 20-23 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር እጅግ ተቆጥቶ ስላረገው የሚናገረው ምንድ ነው?
8. መሳ 3:1-4 እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ያላጠፋበት ቁልፍ ምክንያቶች ምንድ ናቸው?
9. ተተኪው ትውልድ ከገባበት መንፈሳዊ አዘቅት እንዳይገቡ ሊያደርጉ ይችላሉ ብላችሁ የምታስቡት ነገር ምንድ ነው ?
10. ዛሬ ለእኛ ከዚህ ክፍል ጥናት የቀረልን ተግሳጽና ትምህርት ምንድን ነው?
11. በዛሬው የጥናት ክፍላችን መሠረት ስለ ራሳችን፣ስለመሪዎች እና ለተተኪ ትውልድ ጸልየን እንጨርሳለን።

***<u>መደምደሚያ</u>***

እግዚአብሔር ለራሱ ህዝብ ከሌሎች አህዛብ እንዲለዩ ህግ ሰጥቷቸዋል። ይህም መለኪያ ነው። ህዝቡ የአህዛብን መንገድ ሲከተሉ ዋናው የወድቀታቸው ምክንያቸው ነበር።

## መሳ 17:1-21:25

**ማስተወሻ፡-** መሳፍንት ከምዕራፍ 17-21 ታሪካዊ ይዘቱ ከመሳፍንት 1:1-3፡6 ቀጣይነት ያለው ክፍል ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ጥናቶች በመሳፍንት 17-21 ላይ መሥረት ያደረገ ይሆናል:: ከመሳፍንት ምዕራፍ 3:7-16:31 የመሳፍንት መጽሐፍ ጥናት ክፍል ሁለት በሌላ ጊዜ ይኖረናል።

### የዚህ ክፍል አጠቃላይ መግቢያ

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ክፍል በሚቀጥሉት አምስቱ ምዕራፎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል (መሳ 17-21) ። እነዚህም አምስቱ ምዕራፎች ለሁለት ይከፈላሉ ማለትም የመጀመሪያው መሳ 17:1-18:31 ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መሳ 19:1-21:25 ነው:: እነዚህም ሁለቱም ትረካዎች የመጽሐፉ መደምደሚያ ናቸው። ይህ ትረካ እስራኤላዊያን ንጉስ ባልነበራቸው ጊዜ “እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ በነበረበት” ዘመን የነበረውን የሃይማኖት እና የምግባረ ብሉሹነት የቱን ያህል አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር ይገልጻል (17:6, 21:25)።

## የመሳ 17:1-18:31

### መግቢያ

ጸኃፊው በዚህ ክፍል እንደሚናገረው “ሁሉም የራሱን መንገድ ይሄድ ስለነበር” ይህ የመጀመሪያ ትረካ (መሳ 17:1-18:31) የሙሴ ዘር ነኝ በሚለው ሌዋዊ ሰው አማካኝነት በኤፍሬም ምድር ባዕድ ወይም ጣኦትን አምልኮ ማቆሙንና ይህም ለእስራኤላዊያን ወጥመድ በመሆን ወደ ጥፋት እንድመሩ እንዳደረጋቸው ይናገራል። ማለትም

ለእግዚአብሔር ህግ በሙሉ ልብ አለመገዛት ከግለሰብ ወደ ቤተ ሰብ፣ ከቤተ ሰብ ወደ ነገድ ብሎም እንደ ሕዝብ እና እንደ ሀገር ውድቀታቸውን ያሳያል። እንዲሁም በተጨማሪም የዳን ነገድም ርስቱን ትቶ ወደ ሰሜን እስራኤል በሄደ ጊዜ በአህዛብ ልማድ ያደርግ የነበረውን አምልኮ እንዳለ ይዞ በመሄድ ጠኦት አምልኮ ይለማመድ እንደነበረ ይህ ክፍል በግልጽ ይናገራል።

## ጥናት አስር

## የንባብ ክፍል መሳ 17:1-5,6 (ክፍል አንድ)

## ርዕስ፡- ከግለሰብ እና ከቤተሰብ ተጀምሮ ወደ ህዝብና ወደ አገር የተዛመተ ውድቀት

**ዓላማ:-**የአንድ ቤተሰብ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ እና ፈቃድ አለመኖሩ ትተተኪው ትውልድ እና በእግዚአብሔር ሥራ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያመጣ መሆኑን በማሳየት፤በዚህም ዘመን የአንድ ቤተ ሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ምን አስፈላጊ እንደሆነ ማሳወቅ።

**መግቢያ:-** የእስራኤል ህዝብ የታዘዘው የእግዚአብሔር የያህዌን ቃል እንዲኖርና ከእርሱ ብቻ በቀር ሌላ አምላክ በግለሰብ፣በቤተ ሰብና በህዝብም ደረጃ እንዳያመልክ ነው። ይህ በአሥርቱ ትዕዛዛት **በዘጸዓት 19-20** ባለው ክፍል የተወጀ ትዕዛዝ ነው። ለዚህ ደግሞ በግለሰብ፣በቤተ ሰብ እና በህዝብ ደረጃ ተጠያቂነት አለባቸው። መሳፍንት 17:1-5 እንደሚተርከው ሚካ የእናቱን ንብረት በመስረቅ ከአስርቱ ትእዛዛት አንዱን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን የሚካ እናት ራሷ ደግሞ ሁለት አማልክትን እንደምትከተል ያሳያል። ማለትም መኻላዋ እና እርግማኗ በያህዌ ስም ሲሆን ንብረቷን ልጇ ከመለሰላት በኋላ ጣኦት ስታሰራለት ከታሪኩ እንገነዘባለን። ይህ ሁለት ልብ በያህዌ ዘንድ ጸያፊነት አለው ምክንያቱም

ህጉ በጥብቅ “ከእኔ በቀር ሌላ አማላክ አይኑርህ” ይላል። በቁጥር 5 መሠረት ደግሞ ሚካ ለእርሱ ያልተሰጠውን የሃይማኖት ሥርዓት ሲያደርግ እናያለን። የአምልኮና የአገልግሎት ሥርዓት በማከላዊ ቦታ እንዲሆን እና በካህናት እንዲፈጸም ነው።

ሌላው ከዚህ ታሪክ የምንገነዘበው እግዚአብሔር ለአንድ ቤተሰብ የሚሰጠው ስፍራ እና ግምት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው፤ አንድ ቤተሰብ ስልራሱ የቱንም ዓይነት ግምት ሊኖረው ይችላል፤ ይሁን እንጂ የአንድ ቤተሰብ ድርሻ በእግዚአብሔር ታሪክ ውስጥ የሚናቅ አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፤ የአንድ ቤተሰብ ከእግዚአብሄር ፈቃድ እና ሃሳብ ጋር መስማማት ወይም አለመስማማት አይምሮ ሊገምተው ከሚችለው በላይ የሆነ ታላቅ እና ኃይለኛ ነገር ማከናወን ይችላል። ታዲያ ሰይጣን፤ እግዚአብሔር በአንድ ቤተሰብ ሊያደርግ እና ሊሰራ የሚችለውን አሰገራሚና አስደናቂ ነገር ስለሚያውቅ፤ የመጀመሪያውን ጦርነት የከፈተው ቤተሰብን ለማጥፋት ነበር፤ እስከ ዛሬም ድረስ በቤተሰብ ላይ የተከፈተው ይሄ ጦርነት መልኩን እና ስልቱን እየለዋወጠ ተባብሶ የቀጠለ መሆኑ ልብ ሊባል ያስፈልጋል፤ የእግዚአብሔርም ቃል “ እንግዲህ በመጠን ኑሩ ንቁም ጠላታችሁ ዲያቢሎስ  የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራል እና” (1 ጴጥ 5:8)።

**የመሳፍንት 17:1-5,6  ማብራሪያ**

**መሳ 17፡1** የታሪኩ መግቢያ ነው። "ተራራማው በኤፍሬም አገር" የሌዋውያን አገር አይደለም። ይህንን ማወቅ ለታሪኩ ወሳኝ ነው። በኢያሱ 21 መሠረት ለሌዋውያን ከተሰጡት ቦታዎች አንዱ አይደለም። "ሚካ" የሚለው ቃል ትርጉሙ "ማን ያህዌን/እግዚአብሔርን ይመስላል?"

ማለት ነው። እነዚህን ሁለት መነሻዎች ይዘን ነው ይህን ታሪክ ማንበብ ያለብን።

**ቁጥር 2** ሚካ ከእናቱ ብር ይሰርቅና ይመልስላት። የወሰደው ብር 1100 ብር ነው። በዚሁ ምዕራፍ ቁ.10 ላይ እንደምናየው 10 ብር የአንድ ሌላዊ የአንደ አመት ደሞዝ ነው። ስለዚህ ብሩ ለብዙ ዓመታት የሚያኖር ብር ነው። ይህን የሚያህል ብር ወስዶ ሲመልስ ጸጸት የሚባል ነገር አይታይበትም። ምክንያት እናቱ ስትራገም ስለሰማ ነው ሊመልስ ግድ ያለው። "የረገምሽበትም፥ በጆሮዬም የተናገርሽበት" የሚለው የሚያሳየን ምን አልባት እናትየው መስረቁን ገምታ እንዲፈራ ብላ እርሱ እየሰማም ተራግማ ይሆናል። መስረቁ ጸጽቶት ሳይሆን፥ መረገም ፈርቶ ገንዘቡን መለሰላት።

እናቱም በመውስዱ ከመገሥጽ ይልቅ፥ ረገመችው። ሲመልስላትም፥ የመልሰበትንም ልብ ከማስተካከል ይልቅ፥ "እግዚአብሔር ይባርክህ" አለችው። ይህ መልካም ይመልሳል ግን ልጁን የሚያስተካክል አልነበረም።

**ቁጥር 3** የሚካ እናት የተሰረቀውን ብር “የተቀረፀ ምስል አድርጌ ከእጄ ስለ ልጄ ለእግዚአብሔር እቀድሰዋለሁ።” ይህም ሲታይ መልካም ይመስላል። ነገር ግን እርሷም ብሩን መልሳ ለመውስድ ያልፈለገችበት ምክንያት የተረገመ ስለሆነ ይሆናል። ይህ እንኳን ባይሆን፥ ለእግዚአብሔር "እቀድሰዋለሁ" ብትልም "አሁንም ለአንተ እመልሰዋለሁ" ብላዋለች። ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ለምን ለልጅ ይሰጣል? ሚካ ኤፍሬማዊ እንጂ ካህን አይደለም። ለእግዚአብሔር

የተቀደሰን ነገር መቀበል አይችልም። ስለዚህ ንግግሩ መንፈሳዊ የሚመስል ነገር ግን የባአድ አምልኮ ልምምድ የሞላበት ነው።

**መሳ ፲፯፡4** ከተሰረቀው 1100 ብር ውስጥ 200 ብር የተቀረጸ ምስል ተሰራበት። የ"ሚካ" ትርጉም "ማን ያህዌን የሚመስል አለ?" የሚል ቢሆነም፥ በተቀረጻው ምስል ግን ያህዌን "ይህን ትመስላለህ" ብለው በቅርጹ አሳነሱት። ቅርጹንም በሚካ ቤት ውስጥ አኖረችው።

ቁጥር 5 ሚካ በቤቱ "የአምላክ ቤት ነበረው።" የመገናኛው ድንኳን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ቤት "ድንኳኑ" ነው። በከነዓናውያን ዘንድ አንድ ሰው በቤቱ የአምላኩን ምስል አስቀምጦ የቤቱን የተወሰነ ክፍል "የአምላክ ቤት" ሊያደርገው ይችላል። በእስራኤል ግን ይህ ፈጽሞ የተከለከለ፥ የባዕድ ልምምድ ነው። ኢያሱ እኔና ቤቴ እናመልካለን ሲል "እኔም ቤተሰቤም ለእግዚአብሔር እንገዛለን" ማለቱ እንጂ፥ በቤታችን ውስጥ ለእግዚአብሔር ምስል አቁመን፥ መስዋዕት እያቀረብን እናመልካለን ማለቱ አለልነበረም።

በቤቱ የነበረው "የአምላክ ቤት" ባዶ ስለነበር ምስል ጨመረበት። ካስገቡት ምስል በተጨማሪው፥ "ኤፉድና ተራፊም" አስገባ። ገንዘብ ስላለ፥ ሁሉን ማድረግ እንደሚችሉ አሰበው ይመስላል። "ኤፉድና ተራፊም" የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚለዩበት፥ እግዚአብሔር ለካህናት የሰጠው ስጦታ ነው። ይህን መጠቀም የሚችሉት ካህናት ናቸው። ነገር ግን ሚካ ከኤፍሬም ወገን እንጂ ከሌዊ ወገን እንዳይደለ እያወቀ፥ ከልጆቹ አንዱን "ካህን" አደረገው። ይህኛውም ሌላ ጥፋት ነበር። ካህን ከሌዊ ወገን እንጂ ከሌላ ከየትም መመረጥ አይችልም። ካህንም የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ በሊቀ ካህኑ ቀብቶ ነው። ይህን ሁሉ ሚካና እናቱ

ተላለፉ። ባዶ የነበረው “የአምላክ ቤት” ከምስሉ እንዲሁም ከኤፉድና ተራፊም በተጨማሪ ሃሰተኛ ካህን ገባበት።

**መሳ ፲፯፥6** ይህን ሁሉ ያደረጉበት ምክንያት በእነርሱ ዓይን መልካም ያደረጉ እንጂ እግዚአብሔርን እያሳዘኑ እንዳለ እያሰቡ አይደለም። "በዚያ ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።" በዚህ ቤት የምናየው ችግር በሁሉም ቤት አለ። ሁሉም በእግዚአብሔር ቃል መመዘኛ ሳይሆን፥ በራሳቸው "መልካምና ክፉን" መለካት ሲጀምሩ እንዲህ ችግር ይፈጠራል። በዚህ ክፍል "እግዚአብሔር" የሚለው ያህዌን ነው። ማምለክ የፈለጉት የከነዓንን አማልክት አይደለም። ነገር ግን ያህዌን በከንዓን መንገድ ማምለክ ፈለጉ። ይህ ደግሞ የከነዓንን አማልክት ከማምለክ አይተናነስም። በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ዝም ብሎአል። በኢያሱ ጊዜ የነበሩት እስራኤላውያን በኢያሱ 22 እንዳየነው የማይሆን አምልኮ ሲያዩ በሰይፍ ለመቅጣት ተነስተው ነበር። እነዚህስ ይነሱ ይሆን? የዚህን መልስ ከሚቀጥለው ጥናት ጀምሮ እናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመሳ 17፡1-2 መሠረት
    - የምናገኛቸው ባለ ታሪኮች እነማን ናቸው? ሥፍራውስ የት ነው?
    - የዚህ ቤተሰብ አጭር ታሪክ ጭብጡ ምንድን ነው?
    - የእርግማን ቃል ማውጣቷ ስለ ሚካ እናት የሚያመለክተው ነገር ምንድን ነው?

- ሚካ ገንዘቡን የወሰደው እርሱ እንደሆነ እንዲናገር ያስገደደገው ነገር ምንድን ነው?

2. መሳ 17፡ 3-4
   - ሚካ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? እርሱን ተከትላ እናቱ የወሰደችው እርምጃስ ምንድን ነበር? ለምን?
   - በሚካም ሆነ በእናቱ ህይወት እግዚአብሔርን መፍራት ያለ ይመስላችሁሃል? አዎን ወይም አይደለምም ከሆነ ይብራራ?
   - ሚካ እና እናቱ ያደረጉት ነገር ከዘጸ 20:4 አንጻር እንዴት ታዩታላችሁ?
3. መሳ 17፡5 ሚካ ምንአይነት ሰው እንደሆነ የሚያመለክቱ ተጨማሪ መረጃዎች ምንድ ናቸው?
4. በዚህ ታሪክ መሠረት እናትና ልጁ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው መረዳት ችግሩ ምንድ ነው ትላላችሁ? ከአስርቱስ ትዕዛዛት የተላለፉት የትኞቹን ነው?
5. ቁጥር 6 ከቁ.1-5 ካለው ክፍል ጋር ምን ግንኙነት አለው?
6. በዚህ ዘመን የተዘባረቀ ህይወት መኖር ማለት ምን ማለት ነው? እንዴት መላቀቅ እንችላለን?
7. ስለ እግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባውን ጤናማ መረደት ማግኘት እና ህይወታችንን መጠበቅ የምንችለው ከየት እና እንዴት ነው?
8. በአጠቃላይ ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን?

## መደምደሚያ

ሰይጣን ሰውን በፍርሃት ባርነት አስሮ ወደ ጨለማ እና የከፋት መንግስቱ እየነዳ ነው። ፍርሃት ሰው ሊሄድበት የማይፈልገውን መንገድ፣ ሊደርስበትም ወደማፈልገው ርቀት፣ ሊገባበት ወደማይገባውም አዘቅትድ ውስጥ ሊጥለው ይችላል። የህይወት ምንጭ፣ከሞትም ወጥመድ ማምለጫ መንገድ እና ዘመናችንም እንዲረዝም የሚያደርገ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አውቀን መከተል አለብን። እንዲሁም እንደ ግለሰብም ሆነ እንደቤተሰብ እግዚአብሔር እየፈሩ ከመኖር ውጭ ምንም አማራጭ ስለሌለ፤ በእኛና በቤታችን ላይ ፈሪሃ እግዚአብሔር ይሁንልን።

# ጥናት አስራአንድ
## የንባብ ክፍል መሳ 17፡6,7-13 (ክፍል ሁለት)
## የሕዝቡ ወይም የሀገሪቷ ውድቀት በቤተሰብ

**ዓላማ፡-**

የአንድ ቤተሰብ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ እና ፈቃድ አለመኖሩ ትተተኪው ትውልድ እና በእግዚአብሔር ሥራ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያመጣ መሆኑን በማሳየት፤በዚህም ዘመን የአንድ ቤተ ሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ምን አስፈላጊ እንደሆነ ማሳወቅ።

**መግቢያ፡-**

ባለፈው ጥናታችን እንደተመለከትነው በአንድ ቤተሰብ መካከል ለህጉ ያለመታዘዝ የህይወት አቅጣጫ እንዴት እንደቀየረ አይተናል። የቤተሰቡ አባላት ህያው እግዚአብሔርን ከማምለክ እና ከማገልገል ይልቅ፤ በቃሉ እንዳያደርጉት የተከለከለውን በአንጥረኛ ቀልጦ ለተሰራ ምስል በመስገድ በጥፋት እና በአመጻ ጎዳና እየተጎዘ እንደነበር ተመልክተናል። ዛሬም ከዚሁ አጭር የቤተሰብ ታሪክ ቀጣይ የሆነውን እና የመጨረሻቸውን ክፍል እናያለን።

ይሄ በዚህ ቤተሰብ የተጀመረው የአመጻ መንገድ ወዴት ያመራ ይሆን ይህንን በዛሬው ጥናታችን የምንመለከተው ይሆናል።በዚህ ክፍል ሚካ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሳይሆን እርሱ ራሱ የሚፈልገውን አድርጎ በቤቱ ጣኦትን በማምለክ ይኖር ነበር። ሌላው ችግር ደግሞ ምንም እንኳን ሌዋውያን የተጠሩት የእስራኤልን ህዝብ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ቢሆንም (ዘኁልቁ 8:18-22) ብዙዎች የቃሉ አስተማሪዎች እንደሚስማሙት እስራኤላውያን የሌዋውን ኑሮ እየረዱት ስላልነበረ መተዳደሪያ ፍላጋ ቤተልሔምን ለቆ ወደ ኤፍሬም ግዛት ሄዷል።

ሌዋውያን በህዝቡ ስጦታ እንዲተዳደሩ የቃሉ ትዕዛዝ ነበር (ዘኁልቁ 18:24)።

ሚካ ማለት "እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል" ማለት ሲሆን እርሱ ግን የህጉም ይሁን የያህዌን ሙሉ ዕውቀት የለውም። ሚካ ምድራዊ ነገር ብዙ ቢኖረውም እርሱ እንዳሰበው እግዚአብሔርን የመታዘዝ ምልክት አይደለም። በምድር ላይ ብዙ እግዚአብሔርን የማያውቁ ብዙ ምድራዊ ነገር ያላቸው ሞልተዋል።

ሌላው ደግሞ ሌዊውም የሚካን አማልክት ለማገልገል በሚካ መጠይቅ ፈቃደኛ መሆኑ ትልቅ ስህተት ነው። እርሱ ያህዌን ብቻ እንዲያገለግል እንጂ አማልክትን/ጣኦትን እንዲያገለግል አልተጠራም።

የዛሬውን ጥናታችን ካለፈው ሳምንት ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ታሪክ ስለሆነ ያለፈውን ሳምንት ጥናት ልብ ማለት የዛሬውን ጥናታችንን ለማሳለጥ የሚረዳን መሆኑንን ልብ ይበሉ፡፡

## የመሳ 17፡6,7-13 አጭር ማብራሪያ

**መሳ 17፡7፡** በዚህ ቁጥር የምናየው ሰው ወጣት እና ሌዋዊ ነው። በኢያሱ ምዕርፍ 21 እንደምናየው እግዚአብሔር ሌዋውያን በተለያዩ የእስራኤል ክልሎች በዕጣ ተበትነው እንዲኖሩ አድርጎአል።  ዕጣው የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጫ ነበር። በተለያዩ ነገዶች መኃል እንዲኖሩ ያደረገበት ምክንያት ሌዋውያን የእግዚብሔርን ህግ ለህዝቡ እንዲያስተምሩ ነው። በፈልጉበት ሳይሆን፥ ዕጣው በወጣላቸው ቦታ እንዲኖሩ ነው የተወሰነላቸው። ቤተልሔም ግን ለሌዋውያን በኢያሱ ምዕረፍ 21 ከተሰጡት ከተሞች አይደለችም። ይህ ወጣት ግን በቤተልሄም ይሁዳ፥ ለይሁዳ ነገድ በተሰጠው ከተማ ይኖር ነበር። ምንአልባት፥ ቤተሰቦቹ ወደዚህ መጥተው ሊሆን ይችላል ወይም እርሱ

ራሱ ሄዶ ሊሆን ይችላል። ይህን ለሌዋውያን ያልተሰጠችን ከተማ ለቆ ሌላ ቦታ ፍለጋ ሄደ። በእርሱ አመለካከት የተሻለ ቦታ ፍለጋ ለመሄድ ይነሳል። በመሳፍንት ምዕራፍ 17፥6 ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም የመሰለውን ያደርግ ነበር የሚለው፥ ህዝቡን ብቻ ሳይሆን ሌዋውያኑንም እንደሚጨምር ይህ ክፍል ይነግረናል። ምንም እንኳ ስለ አንድ ሌዋዊ እያነበብንም ቢሆንም፥ መሳፍንት ምዕራፍ 17፥6 የሚነግረን ህዝቡም ሌዋውያኑም እንደሚያደርጉት ነው። አሁን ግን ለሌዋውያን ወደተሰጠች ከተማ ይሄድ ይሆን?

**መሳ 17፥8** ጉዞው ግን የወሰደው ሌላ ለሌዋውያን ወዳልተሰጠች ከተማ ነው። በኢያሱ 21፥21 ለሌዋውያን የተሰጠችው የተራራማው የኤፍሬም ከተማ ሴኬም ናት። እርሱ ግን ወደዚች ከተማ ሳይሆን ወደሌላ የኤፍሬም ክልል መጣ። ወጣቱም ወደ ኤፍሬም አገር ወደ ሚካ ቤት መጣ። ምን አልባት በሚካ ቤት ያለው "የእግዚብሔር ቤት" ይታወቅ ስለነበር እርሱን ሰምቶ ሊሆን ይችላል። በምዕራፍ 18 እንደምናየው፥ ምንአልባትም የእንግዳ ማረፊያም ቦታ በሚካ ቤት ስለነበርም ሊሆን ይችላል።

**መሳ 17፥9** የሚነግረን ምንም እንኳ ሌዋዊው እስራኤላዊ ቢሆንም፥ የተራራማው የኤፍሬም ከተማ ነዋሪ ስላይደለ፥ ሚካ አላወቀውም። ስለዚህም "ከወዴት መጣህ?" አለው። ወደፊት ለምናየው ይህ ወሳኝ ስለሆን፥ በልባችን እንያዘው። በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖርን ሰውና የሚሆነው ነገር በዚያ ከተማ ያለ ሁሉ ያውቃሉ።

**መሳ 17፥10** ሌዋዊው የሚኖርበትን ቦታ እንደሚፈልግ ለሚካ ሲነግረው፥ ለምን እግዚአብሔር ወደሰጠው ቦታ እንዲሄድ

አልጠየቀውም። ማንም ስለማንም ግድ የማይሰኝበትም ጊዜ ነው። ይልቁን፥ ከእርሱ ጋር እንዲኖር በር ከፈተለት። “አባት ሁነኝ” ሲለው በእርግጥም አባት ስለሌለው ሊሆን ይችላል። በቁጥር 1-6 ባነበብነው ውስጥ ስለእናቱ እንጂ ስለአባቱ አናነብም። ነገር ግን ሚካ ከሌዋዊው የፈለገው አባትነት “መንፈሳዊ” አባትነትን ነው። ምንም እንኳ ከልጆቹ አንዱን ካህን ቢያደርገውም፥ ካህን ለመሆን የተመረጠው ሌዋዊ እንደሆነ ስለሚያውቅ፥ ሌዋዊውን ካህን ሁነኝ አለው። በአንድ በኩል ልክ የሆነ ቢመስለውም፥ አሁንም እንደገና ስቷል። ይህም ስህተት የሆነበት ምክንያቱ አንደኛ፡ ካህን ማድረግ የሚችል እግዚብሔር ብቻ ስለሆነ፥ እርሱ ካህን ማድረግ ስለማይችል እና ሁለተኛ ሌዋውያን ሁሉ ካህናት ስላይደሉ። ከአሮን ቤት የሆኑ ሌዋውያን ብቻ ናቸው ካህን መሆን የሚችሉት።

የሚበላው፥ የሚለብሰው፥ የሚኖርበትን እና በዓመት 10 ብር ከፍሎ ቀጠረው። ሁሉ ነገር የሙሴ ሕግ ከሚያዘው ጋር ተቃራኒ ነው። ሌዋውያን ደሞዝተኞች አይደሉም።

**ቁጥር 11** ሌዋዊው ምንም እንኳ ለሚካ መንፈሳዊ አባት ቢሆንም፥ ወጣት ስለሆነ ለሚካ “ከልጆቹ እንደ አንዱ ሆነለት” ። ይህ የሚካ አባትነት ግን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች ስለሚያደርግለት ነው።

**መሳ ፲7፡12** ይባስ ብሎ ደግሞ ከኤፍሬም ወገን የሆነው ሚካ፥ ሌዋዊውን ለ"እግዚአብሔር *ሥራ*" ቀደሰው። ሌዋዊው ሚካን ቢቀድስ እንኳ ለአዕምሮ ይመች ነበር፥ ሚካ ግን በገንዘቡ ስለሚያስብ፥ሌዋዊውን “ቀደሰው” ።

**መሳ 17፡13** የሚካ ንግግር የሚያሳየውን በተወሰነ ደረጃ የሙሴን ሕግ የሚያውቅ ያስመስላል። እግዚአብሔር በሌዋውያን እንደሚሰራ ገብቶታል። ስለዚህ በልጁ ፈንታ ሌዋዊውን ካህን ማድረጉ፥ በእግዚአብሔር እንዲባረክ እንደሚያደርገው አሰበ። ነገር ግን ቃሉን ለእርሱ እንዲመቸው እየጠመዘዘና እየተረጎመ እግዚአብሔርን ሊያመልክ አይችልም።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. መሳ 17፡6 በእስራኤል ዘንድ ንጉስ አለመኖሩ ከላይ ስለተጠቀሰው ታሪክ ምን አስተዋጽኦ ይኖረዋል? በሕዝቡ አካሄድ ላይስ ምን ተጽዕኖ ፈጥሯል ትላላችሁ?
2. በመሳ 17፡7-8 መሠረት
   - በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰው ማን ነው? ከየት እና ወዴትስ ነው የሚጓዝ የነበረው?
   - የሚሄድበትስ ምክንያት ምንድ ነው? ከቁ.6 ጋርስ ምን ግንኙነት አለው?
3. በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው መሠረት ዘኁልቁ 18:24 እና 8:18-22 በማንበብ ስለ ሌላዋውያን ምን ተማራችሁ?
4. መሳ 17፡9-12 መሠረት ለሁለቱ ባለታሪኮች የመገናኘታቸው አጋጣሚ የፈጠረው ነገር ምንድ ነው? ወይም ምን አደረጉ?
5. በመሳ 17፡13 በማንበብ ሚካ በሕይወቱ የሚፈጠሩትን አጋጣሚዎች እንዴት ነው የሚረዳቸው?
6. ከዚሁ ክፍል ሳንወጣ ስለ ሚካ ሕይወት ምን እንማራለን? ከእናቱስ ጋር በምን ይመሳሰላል?

7. በዚህ ምዕራፍ በጠፋ ገንዘብ ምክንያት የተጀመረ የታሪክ ሂደት ስለ ደረሰበት ጡዘቱ ተነጋገሩ።
8. ሁሌም የነገሮች መገጣጠም እና ምድራዊ ስኬት እግዚአብሔር በጉዳያችን ላይ አለበት ማለት ይቻላል? ከዚህ ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ምንድ ነው?
9. ከዛሬው ጥናት የተማርነውን አካፍለን በመጸለይ እንጨርሳለን።

## መደምደሚያ

ስህተት አሳቻ መንገድን ይመስላል። አንዳንድ ጊዜ ከመንገዳችን ስተን መሄዳችንን የምናውቀው ብዙ ርቀት ተጉዘን ያላሰብንበት ቦታ ስንደርስ ስለሆነ ነው። እንደዚሁም አንዳንድ ጉዳይ እንዴት እንደተጀመረ እንኳን ሳናውቀው ነገር ግን ሳንስበው ጉዳዩ ያላሰብነውን ቅርጽ የሚይዝበት አጋጣምም ይኖራል። ስለዚህ ለምናስባቸውም ሆነ ለምናደርጋቸው ማናቸውም ነገሮች እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ ያስፈለገናል። እንደዚያ ስናደርግ ህይወታችንን መጠበቅ እንችላለን። እንዲያ ካልሆነ ግን “ምን አለበት” ተብሎ የሚጀመር ትንሽ ነገር ከፍተኛ ጥፋትን ሰንቆ ሊያመጣ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩ አይቀሬ ይሆናል። በመሰረቱ አንድን ነገር ስንጀምር በትክክል ካልጀመርነው በጥሩ ሁኔታ ለመጨረስ ምንም ዋስትና እንደሌለው ግልጽ ነው።

# ጥ ና ት አ ሥ ራ ሁ ለ ት
# የ ን ባ ብ ክ ፍ ል 18፡1-10
# ር ዕ ስ:-የ ማ ህ በ ረ ሰ ብ መ ሣ ት

**ዓላማ**

የአንድ አገልጋይ መሣት አንድን ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን አንድን ማህበረሰብ ሁሉ ሊያስት እንደሚችል አወቀን፥ ለቃሉ ከማይታመኑ አገልጋዮች ራሳችንን እንድንጠብቅ ለማስጠንቀቅ

**መግቢያ**

ባለፉት ሁለት ጥናቶች የቤተሰብና የአገልጋይ መሣትን አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ በአንድ ህዝብ መሃል የነበረውን ማህበረሰብ መሣት እናያለን።

መሳ 18 የሁለት ቀናት ጥናት ይሆናል፡፡ ይህ ጥናት ክፍል አንድ ነው። ይህ ጥናት ዓላማውም ይሁን መግቢያ አንድ ዓይነት ሀሳብ ይሆናል፡፡ ክፍሉም የሚያስረዳን የአንድ ማህበረሰብ ቁጥር የሚጀምረው ከአንድ ቤተ ሰብ እንደሆነ መሆኑን ያስረዳናል። ቤተ ሰብ አንድ ላይ ሲሆን አንድ ማህበረሰብ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ማህበረሰብ አንድ አገር ነው። ባለፉት ጥናቶች አንድ የቤተሰብና የአገልጋይ መሣት ወደ ህብረተሰብ እንደተሸጋገረ አይተናል። የዛሬው ጥናታችን ካለፈው ሳምንት ከተመለከትነው ጥናት የቀጠለ ስለሆነ ያለፈውን ክፍል ማስተወስ ለዛሬው ጥናታችን ይጠቅማል።

## የመሳፍንት 18:1-31 ታሪክ ጭብጥ ሀሳብ

**መሳ 18፡1** በዚህ ምዕራፍ የምናየው የዳን ነገድ የራሳቸውን ቦታ ይፈልጉ እንደነበር ነው። ይህ የሆነው በምዕራፍ 1፡34 እንዳየነው አሞራውያን የዳንን ነገድ ከተሰጣቸው ርስት አባረዋቸው ስለነበር ነው።

ተዋግተው መውሰድ አልቻሉም። ገና ከጅምሩ ልናስተውል የሚገባን ግን፥ በእጣ የተሰጣቸውን ርስት ለአሞራውያን ትተው ሌላ ያልተሰጣቸውን ርስት መፈለጋቸው ችግር መሆኑን ነው። <u>በዚህ ምዕራፍ ውስጥ መልካም የሚመስል፥ ጀግንነት የሚመስል ነገር ብናይ፥ ሁሉም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በገዛ መንገዳቸው በመሄድ ላይ እያሉ የሆነ ነው (ቁ.1)።</u>

**መሳ 18፡2** ሙሴ አስራ ሁለቱን፥ ኢያሱ ሁለቱን ለስለላ እንደላከ ሳይሆን፥ ያለ መሪ አምስት ጽኑዓን ለስለላ ተላኩ። በምዕራፉ ሁሉ እንደምናየው የዳንን ወገን የሚመራ ሌላ ሰው አናይም። እነዚሁ አምስቱ ሰዎች ናቸው ሲመሩ፥ ውሳኔ ሲሰጡ የምናያቸው። ጾርዓና ኤሽታኦል ከይሁዳ ጋር የሚዋሰኑበት የዳን ከተሞች ናቸው። በሶምሶን ታሪክ እንደምናየው በእነዚህ ከተሞች የሚኖሩ የዳን ሰዎች ነበሩ።

**መሳ 18፡3** የሌዋዊውን ድምጽ ያወቁበት አንዱ ምክንያት ከይሁዳ ክልል ስለመጣ ነው። እነርሱም ከይሁዳ ጋር ስለሚዋሰኑ፥ የይሁዳን ሰዎች የቋንቋ ቅላጼ (pronounciation) ያውቁ ነበር። ስለዚህ እንዴት ከይሁዳ ክልል ወደ ኤፍሬም እንደመጣ ጠየቁት።

ቁጥር 4 የሌዋዊው መልስ የሚነግረን ጥቅም ፈላጊ አገልጋይ እንደሆነ ነው። የአግለግሎት ጥሪ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን፥ "አደረገልኝ፥ ቀጠረኝ" ነው መልሱ።

**ቁጥር 5** ይህን ሌዋዊ መጠየቃቸው ገና ሳይነሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳልጠየቁ ይነግረናል። እዚህ ጋር የጠየቁት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይስ አይደለም ሳይሆን፥ ይከናወንልናል ወይ አይከናወንም ነው። ይህ የሚያሳየው ፍላጎታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን፥ መከናወን ብቻ መሆኑን ነው።

**ቁጥር 6** ሌዋዊው እንደጸለየ አናነብም (ቢጸልይም መልስ እንደማያገኝ አስቦ ሊሆን ይችላል)። መልሱ ግን መስማት የፈለጉትን ነው የሚሰሙት። ከቤታቸው ሲወጡ ያልጠየቁት፥ ወስነው እንደመጡ ያውቃል። አይሆንም ቢላቸው እንደማይመለሱም ሊገምት ይችላል። ስለዚህ ይከናወናል፥ በሰላም ሂዱ አላቸው።

**መሳ 18፡ 7** ሌሳ ከእስራኤል በሰተሰሜን ያለ ከተማ ነው። እጣ የተጣለበት ከተማ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው ከተማ አይደለም። እነዚህ ሰላዮች ከዚህ በፊት በሙሴና በኢያሱ የተላኩ ሰላዮች እንዳደረጉት ምንም ሲያደርጉ አናይም። የሌሳ ህዝብ በሰላም የሚኖር፥ ከማንም ጋር ችግርም ህብረትም የሌለው ህዝብ መሆኑ አዩ።

መሳ 18፡8-10 ሰላዮቹ ግምገማቸው ሲያቀርቡ፥ የተወሰኑ የዳን ሰዎች ዝምና ቸል ያሉበት ምክንያት ምናልባት ይህ እርምጃ ልክ እንዳይደለ ስለገባቸው ሊሆን ይችላል ወይም እንደሁሌው ፈሪ ሰልሆኑም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሰላዮቹ ድፍረት የሰጣቸው፥ እግዚአብሔር በእጃችን አሳልፎ ይሰጠናል ያሉበት ምክንያት፥ የሌሳ ህዝብ በሰላም የሚኖር፥ ማንም የማይረዳው መሆኑ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በመሳ 18፡1 መሠረት የምዕራፉ ታሪክ የተከፈተው በምንድን ነው? "ንጉስ አልነበረም" ብሎ መጀመሩ ለታሪኩ ምን አቅጣጫ የሚሰጥ ይመስላችሁሃል? ተወያዩ
2. መሳ 18ከቁ. 2-3 በማንበብ
   - የዳን ልጆች ችግራቸው መፍትሄ ለማገኘት ያደረጉት ነገር ምንድን ነው? ከዚህ የተሻለ ነገር ማድረግ ይችሉ ነበር?

- ጉዞአቸውን ያቀኑት ወዴት ነበር በዚያስ ያገኙት ማን ነበር? ሌዋዊውን የሚካን ካህን በማግኘታቸው ለምን ተደነቁ?

3. መሳ 18፡4-5 በማንበብ ተወያዩ
   - ተደንቀው ለጠየቁት ጥያቄ የሰጣቸው ምላሻ ያስገረማቸው ለምን ይመስልሃል?
   - እግዚአብሔርን እንዲጠይቅላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ምን ነበር? ከሆነ አይቀር መጠየቅ የነበረባቸው ምድን ነበር?
   - የእግዚአብሒርን ፈቃድ ከልባቸው የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው ትላለህ? ከፈለጉ አይቀርስ መቼ እና የት ነበር መጠየቅ የነበረባቸው?
   - ይሄ ጥያቄ በጀመሩት ጉዞ መካከል መነሳቱ፤ ሃሳባቸው ወይንም ጉዞቸው ምን እንዳይሆን የፈለጉ ይመስላል?
4. መሳ 18፡6-7 ሌዋዊው የሚካ ክህን የሰጣቸው መልስ ምንጩ ምንድን ነው ትላለህ?
5. ከቁ. 7 ሰላዮቹ ምድሪቱን ሲሰልሉ ያዩት፤ ካህኑ እንደተናገረው መሆኑ ነገሩን ከእዚአብሔር ነው ማለት ያስችላል? ለምን?
6. ከቁ.8-10 በማንበብ
   - ወደ ወንድሞቻቸው ተመልሰው ያቀረቡት ሪፓርት ፤ የሚያመለክተው ምን እንደሆነና ስለ ውጊያው እግዚአብሔርን አለመጠየቃቸው ምንን ያሳያል?
   - የነገሮች መሰካካት ብቻ እግዚአብሔር ጉዳዩ ውስጥ ለመኖሩ ማረጋገጫ መሆን ይችላል? ለምን?

7. ከዛሬው ጥናት በመነሳት እውነተኛ መንፈሳዊነት ማለት ምን ማለት ነው?

**መደምደሚያ**

የቀደሙት አባቶች ነቢያት እና ሐዋሪያቱም በገዛ ዘመናቸው የእግዚአብሄርን ሃሳብ እና ፈቃድ እንዳገለገሉት ፤ እኛም ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሄር ባሪዎች እና አገልጋዮች መሆን ይገባናል። በተቃራኒው ግን አውቀነውም ይሁን ሳናውቅ እግዚአብሔርን የሀሳባችን እና የአላማችን አገልጋይ ልናደርገው የምንሞክርበት ብዙ አጋጣሚዎች መኖራቸው አይካድም። ይህንና ያንን እንዲያደርግልኝ እና ያንን እንዲፈጽምልኝ የሚሉት የጸሎት ርዕሶቻችን ለዚህ በቂ አስረጂ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ታዲያ በተሰጠን አጭር የምድር ላይ ዘመናችን የአምላካችንን የልቡን ሃሳብ እና ፈቃዱን የምናደርግ እና በሚሰራበት ጊዜም ገንዘቦቹ እንድንሆን ጸጋውን ያብዛልን።

# ጥናት አሥራ ሶስት
# የንባብ ክፍል መሳ 18:11-31
# ርዕስ፦ የማህበረሰብ መሣት
# (በትንሽ ነገር የተጀመረ ስህተት ወደ ህዝብ ተቀየረ)

## ዓላማ

የአንድ አገልጋይ መሣት አንድን ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን አንድን ማህበረሰብና ሀገርን ሁሉ ሊያስት እንደሚችል አውቀን፥ ለቃሉ ከማይታመኑ አገልጋዮች እና ህብረተሰብ ራሳችንን እንድንጠብቅ ለማስጠንቀቅ ነው

## መግቢያ

ይህ ጥናት የመሳ 18 ሁለተኛው ክፍል ነው። ክፍሉም የሚያስረዳን የአንድ ማህበረሰብ ቁጥር የሚጀምረው ከአንድ ቤተ ሰብ እንደሆነ መሆኑን ያስረዳናል። ቤተ ሰብ አንድ ላይ ሲሆን አንድ ማህበረሰብ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ማህበረሰብ አንድ አገር ነው። ባለፉት ጥናቶች አንድ የቤተሰብና የአገልጋይ መሣት ወደ ህብረተሰብ እንደተሸጋገረ አይተናል። የዛሬው ጥናታችን ካለፈው ሳምንት ከተመለከትነው ጥናት የቀጠለ ስለሆነ ያለፈውን ክፍል ማስተወስ ለዛሬው ጥናታችን ይጠቅማል።

## የመሣፍንት 18:11-31 ታሪክ ክፍል ጭብጥ ሀሳብ

**መሳ 18፡11-12** እግዚአብሔርን ሳይጠይቁ ወይም ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ድምጽ ሳይሰሙ ለጥርነት ተዘጋጅተው ሄዱ።

**ቁ..13-20** ጦረኞችን ይዘው ሌዋዊውን አስፈራርተው፥ ሚካን ሳያስፈቅዱ፥ በጉልበት ሌዋዊውንና የአምልኮ መሣሪያዎቹን ሁሉ ወሰዱ። የሌዋዊው "ምን ታደርጋላችሁ" ጥያቄ ሊገሥጻቸው ሳይሆን፥ ስራው

የሚወሰድበት መስሎት ነበር። ስለዚህ እርሱን እንደሚወስዱት ሲነግሩት፥ ከአንድ ቤተሰብ ይልቅ ለአንድ ነገድ አገልጋይ መሆን እንደሚችል ሲነግሩት፥ ስለአገልግሎቱ መስፋት አስቦ፥ ስለሚያገለግለው ሚካ ግድ ሳይለው በደስታ እሺ ብሎ ሄደ።

**መሳ 18፡21-26** ሚካን ያስጮኸው እምነቱ በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን በጣኦቱና በካህኑ ላይ ስለሆነ ነው። ሊያድኑት የማይችሉትን በእጁ የሰራቸውን፥ ለገንዘቡ እንጂ ለእርሱ ግድ የማይለውን አገልጋይ ያለእነርሱ "ሌላ ምን አለን?" አለ። ዳንም በጉልበቱ አስፈራርቶ ሚካን ወደ ቤቱ መለሰው።

**ቁ.27-28** ዳን እግዚአብሔር ስለረዳው ሳይሆን ወይም አብሮት ስለተዋጋ ሳይሆን፥ የሌሳ ህዝብ ተረጋግቶ ተቀምጦ ስለነበርና፥ የሚረዳው ስላልነበረ ነው ያሸነፋት።

**መሳ 18፡29** ዳን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ለምርኮ እስከሰደዳቸው ጊዜ ድረስ የሚካን ጣኦትና ካህን እንደተጠቀሙ ይነግረናል። ካህኑ የሙሴ የልጅ ልጅ መሆኑ ሊሆን ይችላል እርሱን በግድም ቢሆን ለእነርሱ ለማድረግ የፈለጉበት ምክንያት። በእግዚአብሔር ህግ መሰረት ካህን መሆን ባይችልም፥ የሙሴ ዘር ስለሆነ የተለየ ጸጋ ያለው ይመስል፥ የእግዚአብሔር ህግ ተላልፈው ካህን አደረጉት።

**መሳ 18፡30** ዳን በራሱ ክልል የራሱ የሆነ "የእግዚአብሔር ቤትና ካህን" ያደረገው፥ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ እያለ ነው። ይህ የሚነግረን፥ የዳን ወገን እስካሁን ያደረጉት እና የሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንደሆነ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. መሳ 18:11-12 ስለ ዳን ነገድ መንፈሳዊ ችግር ምን እንማራለን? ጦርነቱን እግዚአብሔር የፈቀደው ይመስላችሁሃል? ለምን?
2. መሳ 18፡13-21 በማንበብ በታሪኩ ውስጥ የሆነው ነገር ምንድን ነበር? ከሚካ ቤት ሁሉንም ነገር በግድ መውሰዳቸው ስለ ዳን ነገድ ወይም ህዝብ ምን ያሳያል?
3. የካህኑ ችግር ምን ነበር? ካህኑ በሙሉ ልቡ የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ ይመስላችሁሃል? ለምን?
4. መሳ 18፡22-26
   - የሚካና የዳን ሰዎች ንግግርና ድርጊት ስለሁለቱም ምን ይነግረናል? በተለይ ሚካ "የሠራኋቸውን አማልክቴን ካህኑንም ይዛችሁ ሄዳችኋል፤ ሌላ ምን አለኝ?" የሚለው ንግግሩ ስለአማልክቱና ስለካህኑ ያለውን አመለካከት እንዴት ይገልጠዋል?
   - ከቁ.24 ምን ተማራችሁ? ሰው የራሱን አምላክ ሊሰራ ይችላል? እንዴት?
5. መሳ 18፡27-29 መሰረት የዳን ነገድ አሸንፈው መውረሳውቸውን ይተርካል። በዚህ መሠረት
   - መሬቱን መውረሳቸው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለመሆኑ ማስረጃ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
   - ወራሹም (የዳን ነገድ) ተወራሹም (የላሳ ወይም የላይሻ ሰዎች) የእግዚአብርሔርን መንገድ የመከተላቸው ወይም ያለመከተላቸው ምን ማስረጃ አለ?

6. መሳ 18፥30-31 በማንበብ

- የእግዚአብሔር ቤት በሴሎ እያለ የዳን ወገን የተቀረጸውን ምስል ማቆማቸው ስለ ዳን ነገድና ስለ ካህኑ ዮናታን ምን ያስተምረናል?

7. በዛሬው ጥናት ሃሳብ መሰረት ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን አካሄድ በጋር እንጸልይ

**መደምደምያ**

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሆነን ልናከናወን ስለምንችል፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ እየኖርን መሆናችንን በክንውናችን ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል ልንፈትን ይገባል።

# ጥ ና ት አ ሥ ራ አ ራ ት

## የሚቀጥሉት ጥናቶች በመሳ 19:1-21:25 መሠረት ያደረገ ይሆናል።

## የዚህ ክፍል አጠቃላይ መግቢያ

**መሳ 19:1-21:25** የመጽሐፉ መደምደሚያ ሁለተኛ ትረካ ነው። በዚህ ክፍል የጊብዓ ሰዎች የፈጸሙት ድርግት እስራኤላዊያን በሥነ ምግባር ረገድ ምን ያህል እንደ ወደቁ የሚያሳይ ታሪክ ነው። ይህም ምን ያህል ከእግዚአብሔር እንደራቁ ያሳያል። ውድቀታቸውም ከብዙ ዘመን በኋላ በሆሴዕ ትንቢት ተመዝግቦ ይገኛል (ሆሴ 9:9፣10:9)። የከተማይቱ ክፋት ከሌሎቹ የከነዓን ከተሞች አንሶም ይሁን በልጦ ባይገኝም እግዚአብሔር በእስራኤላዊያን አማካኝነት ሊያጠፋቸው ፈልጎ ሳለ የብንያም ነገድ ልጆች ግን የገዛ ወገናቸው እስኪያልቁ ድረስ ለጊብዓ ሰዎች በመርዳት ተዋጉ። የእስራኤል ህዝብ ለምን እንደተጠሩና ለማን እንደሚኖሩ ባለማወቅ በታላቅ ውድቀት ላይ የነበረው ህዝብ መሆኑን ያሳያል።

## መሳፍንት 19:1-30

## ርዕስ፦ የ ራ ስ ወ ዳ ድ አ ገ ል ጋ ይ ድ ር ጊ ት ና የ ህ ዝ ቡ የ ው ድ ቀ ት ው ጤ ቱ

**ዓላማ፦**

የእግዚአብሔር ክብር ሲነካ ግድ የማይላቸው፥ ነገር ግን የራሳቸው ክብርና ጥቅም ሲነካ የሚያስቆጣቸው አገልጋዮችም ይሁኑ ምዕመናን እንዳሉ ለማስታወስና እንዲሁም አገልጋዮችን በህይወታቻው፣ በሥራቸውና በንግግራቸው እየመዘንን እንጂ አገልጋይ ነኝ ስላሉ ብቻ እርስ በእርስ ሊከፋፍሉን ሲሉ ልንሰማቸው እንደማይገባ ለማሳየት

**መግቢያ፡-**

የአንድ አገልጋይ በትምህርትና በኑሮው መሳት፥ በቤተሰብም በማህበረሰብም ደረጃ መሳት እንደሚያመጣ በባለፉት ጥናቶች አይተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ አንድ አገልጋይ ህዝብን ለመምራት የተሰጠውን የመሪነት ጸጋ ህዝብን በህዝብ ላይ ለማስነሳት ሊጠቀምበት እንደሚችል ለማሳወቅና፥ አገልጋዮች የሚሉትን በመማመዛዘን መስማት እንዴት እንደሚገባን እናያለን። አገልግልጋዮ እንደ እግዚአብሔር ቃል አለመኖር ወይም አለመታዘዝ ለህዝብ መተላለቅ ምክንያት ሊሆን ይሸላል።

## የመሳ 19:1-30 የታሪኩ ጭብጥ ነገር

**መሳ 19:1** “በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ በሌለበት ጊዜ …” ማለት ሰው ሁሉ የያህዌ ህግ የሚለውን ሳይሆን የፈለገውን ጣኦት ማምለክንም ጭምር ማድረግ ነው።

ጸኃፊው ንጉስ የሚለው እግዚአብሔርን አለመፍራት ስላለ ሁሉም ወደ አከባቢው ሰዎች ጠኦት መዞራቸውን የሚያሳይ ትምህርት ነው። ማለትም በኢያሱ ዘመን የገቡትን ቃል ኪዳን ማፍረሳቸውን የሚያሳይ ታሪክ ነው።

በአዲስ ኪዳን ጠኦት ምንድ ነው? “የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።ልጆች ሆይ፥ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ” (1ዮሐ 5:20-21)

“ በእነዚህም መቅሠፍቶች ያልተገደሉት የቀሩቱ ሰዎች ለአጋንንትና ያዩ ወይም ይሰሙ ወይም ይሄዱ ዘንድ ለማይችሉ ከወርቅና ከብር ከናስም ከድንጋይም ከእንጨትም ለተሠሩ ለጣዖቶች እንዳይሰግዱ ስለ እጃቸው

ሥራ ንስሐ አልገቡም፤ ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም” (ራዕይ 9፡20-21)

**መሳ 19:2** ይህ ቁጥር የቁጥር 1 ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህች ቁባት ለሌዋዊው አለመታመኗን በግልጽ ይናገራል። ህዝቡ በግልም ይሁን በማህበር በሁሉም መንገድ አመንዝራ ነበር። ወደ ጣኦት መሄድ ምንዝርና እንደሆነ ቃሉ ብዙ ቦታ ተናግሯል (ሆሴ 1:2)።

**መሳ 19:3-9** ያልታመነችው ቁባት ከሄደችበት ከሀገሯ ለማምጣት ሌዋዊው እንደሄደ ይህ ክፍል ይናገራል። በዚህ ክፍል ጸኃፊው የአባቷንና የየሌዋዊውን እንግድነት እና አብሮ መደሰትን እንጂ አብራው ለመመለስ እስከተነሳችበት ጊዜ ድረስ ብቻ እንጂ ሴትቱ የት እንዳለችም አይናገርም። በእርግጥ የቁባቷ ህይወት ለአባቷም ቢሆን ክብር አልነበረም።

**መሳ 19:10-21** የብንያማዊያን የሞራል ግሸበት (የያህዌን ህግ አለመታት ውድቀት ፍሬ)

ብንያም ከ12ቱ የእስራኤል ነገድ አንዱ ነው። ሀገሩ አይሁዳዊያን ወይም ብንያማዊያን እና ሌሎችም የጊብዓ ሰዎች እግዚአብሄርን ባለመታዘዝ በውድቀት የነበረ ህዝቦች ናቸው። ሌዋዊው ቁባቱን ይዞ በመመለስ ላይ እያለ ሲመችበት ኢያቡሳዊያን (የእስራኤላዊያን ያልሆኑ ህዝብ) ማደር ባይፈልግም ለማደር የደርሰበት ቦታ የነበሩ እስራኤላውያን በሥነ ምግባርን እና በባህርይ እጅግ የተበላሹ እንደ ነበሩ ያሳያል። በእርግጥ ኢያቡሳዊያን በመሳ 1:21 መሠረት የብንያም ነገድ ፈጽሞ ማውጣት ወይም ማጥፋት ሲገባቸው የተውአቸው ህዝብ ነው። መሳ 19:15 እንደሚያመለክት የጊብዓ እና ብንያማዊያንም ቢሆኑ አልተቀበሏቸውም። በዚህ ክፍል እንግድነቱን የተቀበለው ብንያማዊያን ሳይሆን መጤው እስራኤላዊ ነው (ቁ.19-20)።

**መሳ 19:22-28** የቀጠለ የብንያማዊያን የሞራል ግሸበት (የያህዌን ህግ አለመታት ውድቀት ፍሬ)

ሌዋዊውን አብረውት ያሉትን እንግዳ የሚቀበል ሰው ቢገኝም የሰዶም እና ገሞራ ታሪክ እንደተደገመ ክፍሉ ይናገራል። ክፍሉ ወስላቶች የሚላቸው ሰዎች በቀጥታ ለመርከስ የጠየቁት ወንዶቹን ቢሆንም በሽማግሌው ብርታት ዓመጹ ሌሊቱን ሁሉ የተፈጸመው በቁባቷ ላይ እንደሆነና ቁባቷንም በደጅ አምጥተው እንደጣሉ ታሪኩ ይነግረናል። ሌላው በዚህ ክፍል ከባድ የእርስ በርስ ጦርነት ማነሳሻ ጭካኔ የተፈጸመው በሌዋዊው ቁባቱን 12 ቦታ መቆራረጡ እና ጠብን በአደባባይ መጥራቱ ነው። ጠቡ እንድካሄድ ያነሳሳው በሁሉም የእስራኤል ወንድሞች መካከል ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. መሳ 19:1 መሠረት "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ በሌለበት ጊዜ …" የሚለውን ሀሳብ ጸኃፊው በዚህ ክፍልም መድገም ለምን አስፈለገ?
2. መሳ19: 2 በማንበብ በዚህ ቁጥር የተጠቀሰችው ቁባት ህይወቷና ድርግቷ ከቁ.1 ጋር እንዴት ይገናኛል?
3. መሳ19:3-9 በማንበብ ከክፍሉ የተረዳችሁበትን ነገር ተወያዩ?
4. መሳ 19፡10-14 ሌዋዊው አገልጋይና ከቁባቱ ጋር በጉዞው የገጠመውን ነገር ተወያዩ?
5. መሳ 19:15 በማንበብ ብንያማዊያን መንገደኛውን ሌዋዊ እንግድነት ያልተቀበሉት ምክንያት ምንድ ነው? ለም?
6. መሳ 19:16-21 መሠረት አርሶ አደሩ ሽማግሌ ለመንገደኛው ሌዋዊ ስላደረገለት ነገር ተነጋገሩ?
7. መሳ 19:22-27 በማንበብ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው

- እንግዶቹ ምን ገጠማቸው?
- ይህ ታሪክ ከሰዶም እና ከገሞራ ሰዎች ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ተወያዩ (ዘፍ 19:1-6)። የሰዶም ሰዎች እስራኤላዊያን አልነበሩም ነገር ግን የጊብዓ ሰዎች ብንያማዊያን/እስራኤላዊያን ናቸው። ይህ ደግሞ ምን ያሳያል?

8. በመሳ 19:28-30 መሠረት
   - በቁባቱ ላይ በደረሰባት ነገር ምክንያት ሌዋዊው የወሰደውን እርምጃ አብራሩ?…
   - የወሰደው እርምጃስ ምን ውጤት እንዲያመጣ አስቦ (ፈልጎ) እንደሆነ ተወያዩ። ይህስ ስለ ሌዋዊው ምን ያሳያል?
9. በዚህ ዘመን ስላሉ የሞራል ውድቀቶች ተወያዩ። የሞራል ውድቀት መሠረቱ ምንድ ነው?
10. የሥነ ምግባር እና የሞራል ውድቀትን ለመከላከል ቤተ ክርስቲይን ምን ኃላፊነት አለባት እኛስ?

***መደምደሚያ***

ትክክለኛ የሥነ ምግባር ኑሮ ለመኖር የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና ማድረግ አማራጭ የለውም። በራስ መንገድ መሄድ ውድቀትን ያስከትላል። ለሌሎችም ጥፋት ምክንያት ይሆናል።

# ጥናት አሥራ አምስት

# የምንባብ ክፍል መሳ 20:1-48

# ከእግዚአብሔር በተሰጠ ትዕዛዝ ወጥ በሆነ ሕይወትመኖር

**ዓላማ:-**

ቃሉ ከሚያስተምረን ውጪ ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ ሳንል ጌታን ብቻ በመከተል እንድንኖር ማስተማር-ጣኦትን ማራቅ እና ከጣኦት መራቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። እውነት አንጻራዊ እና እኛ እንደፈለግነው የምናደርጋት ነገር አይደለችም።

**መግቢያ**

የሌዋዊያን ጥሪ በማደሪያ ድንኳን ዙሪያ ያሉትን አገልግሎቶችን መፈጸም እና ሕዝቡን ማገልገል እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል። ይሁን እንጂ በመሳፍንት ዘመን መሪ ባለመኖሩ ምክንያት ሰው ሁሉ በዓይኑ ፊት ደስ ያለውን ስለሚያደርግ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሌዋዊ በራሱ መንገድ ሲሄድ ሳለ በገጠመው ችግር ምክንያት በእስራኤል ልጆች መካከል ስለተነሳ ጦርነት እና እልቅት መነቻ ምክንያት ሆኗል። የዛሬውን ጥናት ለመቀጠል የባለፈውን ጥናት ማስታወስ አስፈላጊ ነው (መሳ 19)።

## የመ ሳ 20:1-48 አጭር ማብራሪያ

መሳ 20:1-7:- ይህ ምዕራፍ ከምዕራፍ 19 የቀጠለ መሆኑን እናውቃለን። በመሳ 20:1-7 የእስራኤል ህዝብ በምዕራፍ 19 ላይ ባለው ታሪክ መሠረት በሌዋዊው አነሳሽነት 12ቱም ነገድ ገላዓዳውያንንም ጨምሮ ለጥሩ ነገር ያልተነሱትን ያህል ለጥፋት በአንድ ልብ ሆነው 400ሺ ተዋጊዎችን አዘጋጁ። በዚህ ክፍል ሌዋዊውም የሆነውን ነገሩን

አብራራላቸው። እርሱም ለጦርነት አነሳሳቸው።እግዚአብሔር መጠየቅ የለም።

**መሳ 20:8-17** ይህ ክፍል እንደሚገልጸው አሁንም የብንያምን ነገድ ለማጥፋት እንደ አንድ ሰው ሆነው ስልቶችን መቅረጽ ጀመሩ። የብንያምም ነገድም ጥፋተኞችን እንዲያወጡ ቢጠየቁም ማውጣት አልፈለጉም። በኢያሱ ጊዜ በጋይ መሸነፍ ምክንያት የነበረውን የአከዓብን ቤተ ሰብ ማጋለጥ ጋር ሲነጻጸር ይህ ተቃራኒ ነው (ኢያሱ 7)። የብንያምም ነገድ ይሁን ሌሎች ነገዶችም በእግዚአብሔር ፊት አለመታዘዝ እያሳዩ የነበሩበት ወቅት ነው። ሁለቱም ለጦርነት ተዘጋጁ። እርስ በእርስ ለመጠፋፋት መዘጋጀት የአለመታዘዝ ውጤት እንጂ የእግዚአብሔር ሀሳብ አይደለም።

**መሳ 20:18-25** በዚህ ክፍል እስራኤላዊያን ለጦርነቱ እግዚአብሔር ተመላልሰው ሲጠይቁ እና ብንያማውያን ግን እግዚአብሔርን ምንም እንደማይጠይቁ ወይም እንደማይፈልጉ ይታያል። በክፍሉ ብዙ እስራኤላዊያን በጦርነቱ መውደቃቸውም ተጠቅሶ ይገኛል። በተጨማሪም ለጸሎት ቢቀርቡም የጸሎታቸው ጥያቄ ወንድሞቻቸውን መወጋት ነበር (ቁ.18 እና 23)። እግዚአብሔርም ለምኞቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው።

**መሳ 20:26-47** በዚህ ክፍል ይህ ታሪክ በሚሆንበት ወቅት ታቦቱ በመካከላቸው እንደነበረና ሊቀ ካህኑም የአሮን የልጅ ልጅ ፊንሐስ እንደነበር ማስታወስ ለብዙ ነገር ይጠቅማል (ዘኁ.25)። በመሳፍንት ምዕራፍ አንድ አከባቢ የሆነ ታሪክ ነው ማለትም ከኢያሱ ሞት በኋላ ብዙም ሳይቆይ የሆነ ነገር ነው:። ምክንያቱም መሳፍንት በአጠቃላይ ከ300-350 ዓመታትን ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ነው። ይህ የሚያሳየን

የመሳፍንት መጽሐፍ ምዕራፎች በጊዜ ቅደም ተከተል የተጻፈ እንዳልሆነ እንድናውቅ ይረዳናል።በተጨማሪም በቁ. 35 “እግዚአብሔር ብንያምን በእስራኤል ፊት መታው፤” የሚለው ቃል አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ይህ ቁጥር የሚያሳየው እግዚአብሔር እንደ ሰዶም እና ገሞራ የብንያምን ሀገር እንደመታ ነው። የብንያም ሀገር በሰዶም እና በገሞራ ኃጢአት (ሰዶማዊነት) እጅግ ረክሶ ነበር። ከ600 ሰዎች ውጪ ብንያማውያን ሁሉ አለቁ። ትልቅ ጥፋት ተሠራ።

**የመወያያ መጠይቆች**

1. መሳ 20:1-11 መሠረት
   - እስራኤላዊያን እንደ አንድ ሰው ሆነው የተሰበሰቡት ምክንያት ምንድ ነው?
   - በእግዚአብሔር ፊት የመቆማቸው ምክንያት ለምንድ ነው ትላላችሁ?
2. መሳ. 20፥12-13-
   - በዚህ ክፍል መሠረት  የብንያም ነገድ ከወንድሞቻቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት የእምቢታ ምላሽ ምክንያት ምንድ ነው? ስለ ሕይወታቸውስ ምን ያሳያል?
3. መሳ 20፥14-17 መሠረት የብንያም እና የእስራኤል ልጆች የኃይል አሰላለፍ (የተዋጊዎች ቁጥር) እንዴት ነበረ? በሰው ግምት ስለ ጦርነቱ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ያስረዳል?
4. መሳ 20፥18-28  መሠረት
   - እስራኤላዊያን በቤቴል ተሰብስበው እግዚአብሔርን የጠየቁት ጥያቄ ምንድ ነበር?

- እስራኤላዊያንን እግዚአብሄር “ወደ ጦርነቱ ወጡ” ብሏቸው ከአንዴም ሁለቴ የተሸነፉበት ምክንያት ምንድ ነበር?
- እስራኤላዊያን ለእግዚአብሔር ማቅረብ የነበረባቸው ጥያቄ ምን ነበር?
- መሳ 20፡26-28 በመመልከት የእስራኤል ልጆች ካደረጉት ነገር ከባለፉት ውድቀቶች ምን የተማሩ ይመስላችሁሃል?

5. በመሳ.20:29-48
   - በማንበብ የሆነውን ታሪክ አብራሩ?
   - በዚህ ክፍል እስራኤላዊያን ብንያማውያንን ሲያሸንፉ እና የብንያም ነገድ ዘር የማጥፋት ድረስ ሲሸነፉ እናያለን። በዚህ የወንድማማቾች ግጭት በማሸነፍ እና በመሸነፍ ሂደት ማን ጻድቅና ማን ኃጢአተኛ ይመስላችሁሃል? ለምን?
6. ከዛሬው ጥናት ወይይት ምን ተማርን።

**መደምደሚያ**

የእግዚአብሔርን መንገድ አለመከተል ከወንድም ወይንም ከወንድሞች ጋር መጠፋፋትን ያመጣል። ስለዚህ እግዚአብሔርን በመከተል አብረን መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው።

# ጥናት አሥራ ስድስት

# የንባብ ክፍል መሳ 21፡1-25

# በእግዚ አብሔር ትዕዛዝ ብቻ አለመኖር ግራ የመጋባት ሕይወት ነው

**ዓላማ፡-**

ቃሉ ከሚያስተምረን ውጪ ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ ሳንል ጌታን ብቻ በመከተል እንድንኖር ማስተማር-ጣኦትን ማራቅ እና ከጣኦት መራቅ እንዲሁም እውነት አንጻራዊ እና እኛ እንደፈለግነው የምናደርጋት ነገር አለመሆኗንም ማሳየት።

**መግቢያ፡-**

መሳፍንት 21 በአጣቃላይ የሚነግረን የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ማጣት ውጤቱ ትልቅ ግራ መጋባት የሚታይ ምዕራፍ ነው። ግራ የመጋባቱም ውጤት በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን ያለመከተል ዋጋ ነው። የእውነተኛ መንፈሳዊ ሰው ውሳኔ ለመወሰን ትክክለኛ የደቀ መዝሙር ህይወት ያስፈልጋል። ብዙዎቻችን እንደሚናውቀው “ በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም፤ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር” (መሳ 17:6)። በዚህ ምክንያት በምዕራፉ የሆኑ ውጤቶች ትልቅ አሳዛኝ ነው። የዛሬውን ጥናት ለመመልከት እንዲረዳን በመሳ 20 ላይ የተመለከትናቸውን ነገሮች ማሰብና ማያያዝ በጣም ጥሩ ይሆናል።

## የመሳ 21፡1-25 ታሪክ አጭር ማብራሪያ

**መሳ 21:1-8 ቁ. 1፣ ቁ.6 እና ቁ. 18** ሁሉም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባለመከተል ምክንያት ባለማስተዋል እና በስሜታዊነት የዘሩትን ብዙም ሳይቆይ ማጨድ ጀመሩ። መሳ 21:6 “የእስራኤልም ልጆች ስለ

ወንድሞቻቸው ስለ ብንያም ልጆች ተጸጽተው፡- ዛሬ ከእስራኤል አንድ ነገድ ጠፍቶአል" (መሳ 21:6) አሉ። የዚህ ክፍል ችግር የብንያምን ነገድ ጨርሶ የማጥፋት እቅድ መሃላ ነበር። ከመሳፍንት አንዱ ዮፍታሄ የሚባል መስፍን ያለ እግዚአብሔር እውቀት ስለት ተሳለ ይህም ልጁን በሞት በማጣት እጅግ ሀዘን ውስጥ እንደከተተው ይታወቃል (መሳ 10:31-35)። ከዚህ በፊት በብንያማዊያን መሸነፋቸው አስለቅሶአቸው ነበር አሁን ደግሞ የብንያም ነገድ ዘር ሊጠፋ ስለሆነ ለቅሶ ጀመሩ። እንደፈለጉት የሚኖሩ መሆናቸውን ከዚህ በቀላሉ ማየት ይቻላል። ስሜታቸው እንደመራ ይኖሩ ነበር። በግማሽ እውቀት እና ልብ ለ እግዚአብሔር ለመገዛት መሞከር ትልቅ ጉዳት አለው። ኃጢአትን በሌላ ኃጢአት ለመሸፈን መሞከር ውድቀቱ ብዙ ነው።

አሁንም ለብንያም ወንዶች ልጆች ሚስት ለማግኘት በመሳ 21፡5 የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ወደ ምጽጳ ስላልወጣ ሰው፡- እርሱ ፈጽሞ ይገደል ብለው ታላቅ መሐላ ምለው ነበርና፡- ከእስራኤል ነገድ ሁሉ ወደ ጉባኤ ወደ እግዚአብሔር ያልወጣ ማን ነው? አሉ።" አሁንም ሌሎችን የመግደል ፕሮግራም ሲያጡ ይታያሉ። በዚህም ምክንያት ከኢያቢስ ገለዓድ ያልወጡትን ከደናግሎች በስተቀር ሌሎቹ እንዲገደሉ ት ዕዛዝ ተሰጣቻው። እነርሱም ተገደሉ። በዓይናቸው ፊት ልክ የመሰለውን ነገር ብቻ ያደርጉ ነበር።

**መሳ 21:9-15 ቁ. 15** እንዲህ ይላል "እግዚአብሔርም በእስራኤል ነገድ ውስጥ ስብራት ስላደረገ ሕዝቡ ስለ ብንያም ተጸጸቱ"፣ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር በፊጹም ልቡ ካልተመለሰ በስተቀር እና እግዚብሔርም ካላስተካከለው በስተቀር የሰው ልጅ ከስህተት ወደ

ስህተት ይሸጋገራል። የብንያም ነገድ ወንዶች ሚስት ያገቡበትም መንገድ ትክክለኛ አልነበረም።

**ማጠቃለያ፡-**

**መሳ 21:16-25** በዚህ ክፍል ደግሞ ለተቀሩት ለብንያም ወንዶች ልጆች የማኅበሩ ሽማግሌዎች ሚስት የሚያገኙበትን የተሳሳተ ምክር እየመከሩአቸው ይታያሉ። ማለትም በጠለፋ ሚስት እንዲያገቡ እየመከሯቸው ይታያሉ። መሳ 21፡25 የመሳፍንት ታሪክ ጸኃፊ ታሪኩን ሲደመድመው በ17:6 በጀመረው ነገር ይጨርሳል። ማለትም እንደሚከተለው ይላል፡- "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" (መሳ21:25)። ይህም ብቻ ሳይሆን በመካከልም በ18:1 እና በ19:1 ይህንኑ ይደግማል። ጸኃፊው አሁንም ህዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንደተመለሱ ተናግሮ ሳይሆን የሚጨርሰው ሁሉም በዓይኑ ፊት መልካም መስሎ የሚታየውን እንደሚያደርግ አሳይቶ ይጨርሳል። ምሳሌ 14:11-12 እንደሚከተለው ይላል "11 የኀጥኣን ቤት ይፈርሳል፤ የቅኖች ማደሪያ ግን ያብባል። 12 <u>ለሰው ቅን የምትመስል</u> <u>መንገድ አለች፤ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው" (</u>ምሳሌ 14:11-12)::
እውነት አንጻራዊ አይደለች! ነው። ግለሰቦች በስሜታቸው ተነስተው የሚያስተምሩት ተምህርትም አይደለም። እውነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ብቻ ነው።**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. መሳ 21:1 መሠረት በድጋሚ የእስራኤል ልጆች የተሰበሰቡበት ምክንያት ምን ነበር? ተነጋገሩ

2. መሳ 21:1-4 መሠረት ተሰብሰበው ያደረጉትና ላደረጉት ነገር ዋና ምክንያት ምን ነበር?
3. መሳ 21:5 መሠረት እስራኤላዊያን የገጠማቸውን ችግር ሊፈቱበት ስለሚሄዱበት መንገድ ምን ያሳየናል
4. መሳ 21:6 በማንብበ በብንያማዊያን ላይ ስለተጋረጠው አደጋ እስራኤላዊያን በእውነት የተጸጸቱ ቢሆን ኖሮ መውሰድ የነበረባቸው እርምጃ ምን ነበር ትላላችሁ?
5. መሳ 21:7-18 ክፍል ስናይ
    - መጀመሪያ ላደረጉት ጥፋት መፍቴሔ ብለው ያሰቡት እና ያደረጉት ተጨማሪ ጥፋቶች ምንድ ናቸው?
    - በሂደቱ የእግዚአብሔር ድርሻ ነበረበት ትላላችሁ? ለምን
6. መሳ 21:19-24 ስህተትን በሌላ ስህተት ለማረም ስለሄዱበት ርቀት ተነጋገሩ። የእንደዚህ ዓይነት አካሄድ ችግሩ ምንድ ነው?
7. መሳ 21:25 መሠረት የዚህንም ምዕራፍ ይሁን አጠቃላይ የመጽሐፉን ዋና ሀሳብ ጠቅልሎ የሚያስረዳው እንዴት ነው? ተወያዩ።
8. አንድ ሰው እግዚአብሔርን ፈልጋለሁ እያሉ ነገር ግን የገዛ ሀሳብናና ፈቃዱን እያደረገ ስለመጓዙ ታቃርኖ ምን እንማራለን?
9. አንድን ስህተት በሌላ ስህተት ማረም እንደሌለብን ከራሳችን ህይወት ምሳሌ በማቅረብ ተነጋገሩ።
10. ዛሬ በዚህ ባለፉት ጥናቶች ጌታ ስላስተማረን እርሱን እናመሰግናለ

**መደምደሚያ**

“እስራኤል በዓይኑ ፊት መልካም መስሎ የታየውን ማድርግ” ብዙ ውድቀትን አሳጭዷል። ዛሬም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የመዳን መንገድም ይሁን የሥነ ምግባር መንገዱ አንድ ብቻ እንደሆነ ያስተምረናል። እርሱም ክርስቶስ ብቻ ነው። እውነት አንጻራዊ አይደለችም።እኛ መኖር ያለብን እኛ እንደፈለግነው ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ቃሉ እንደሚለው መሆን ለሕይወታችን ጠቃሚ ነው።ቃሉን ለማወቅ ሁል ጊዜ ተማሪ መሆን አስፈላጊ ነው። የተማርነውን መኖርም የጌታ ቃል ያዘናል። በእኛ ዓይን ፊት መልካም መስሎ ከሚታየን ማንኛውም ሀሳብና ድርጊት እግዚአብሔር ይጠብቀን እንዲሁም እኛም ለቃሉ በመታዘዝ መኖር እንዳለብን ልናውቅ ይገባናል።

ማንኛውም አስተያየት ካላችሁ በመሪዎቻችሁ

በኩል አሳውቁን

ተባረኩ!

“ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት ሲኖሩ፣
እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ ያሰኛል!
በራስ ላይ ፈሶ፣
እስከ ጢም እንደሚዘልቅ፣
እስከ አሮን ጢም እንደሚወርድ፣
እስከ ልብሱም ዐንገትጌ እንደሚደርስ ውድ ሽቱ ነው።
ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ እንደሚወርድ፣
እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤
በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን፣
ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዞአልና” (መዝ 133፡1-3)።

# ክፍል ሁለት ጥናት

(መሳፍንት 3፡7-16:31)

በሌላ ሕትመት ይቀጥላል